# በትምህርት ቤት ውስጥ በጤና እና ሥነ-ንፅህና የባህሪ ለውጥ ለማምጣት የሚደረጉ ጨዋታዎች

## የማሰልጠኛ & የመተግበሪያ መመሪያ

የደ.ብ.ብ.ሕ.ክ አክስለሬት ፕሮግራም

ቅጅ 1.0: የካቲት 2013ዓ.ም

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

NALA

Sightsavers

# ማውጫ

ለአመቻቾች ማስታወሻዎች ........ 6

ክፍል 1፡ ስለ ትራኮማ ማስተማር ........ 9

1.4 ትኩረት: የማስተማሪያ ዘዴዎች (style) ........ 12

ክፍል 2፡ በሽታን መከላከልና የባህሪ ለውጥ ማምጣት ........ 15

2.4 በርካታ ነገሮችን በአንዴ የማድረግ/የአስተሳሰብ ክህሎቶች ........ 20

ክፍል 3፡ ታሪኮችን (ተረቶችን) በመንገር ግንኙነቶች መገንባት ........ 24

3.2 የልጅነት እድሜ ........ 24

ክፍል 4፡ ለማነሳሳት እና ግብ-ለማስቅመጥ የሚሆኑ ጨዋታዎች ........ 29

4.2 በክፍል ውስጥ ጨዋታዎችን መጠቀም ........ 30

ክፍል 5፡ እቅድ ማዘጋጀት ........ 35

አባሪ 1፡ የእጅ አስተጣጠብ ሂደቶች ........ 38

አባሪ 2፡ እጅን መታጠብ + ፊትን መታጠብ ........ 39

አባሪ 3፡ በወረዳ ደረጃ የድርጊት መርሃ-ግብር ........ 40

አባሪ 4፡ በትምህርት ቤት ደረጃ የድርጊት መርሃ-ግብር ........ 41

አባሪ 5፡ በወረዳ ደረጃ የክትትል ቅጽ ........ 42

አባሪ 6፡ በትምህርት ቤት ደረጃ የክትትል ቅጽ ........ 44

መመሪያውን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የዋሉ ማጣቀሻዎች ........ 46

ይዘት: ናላ ፍውንዴሽን

©2013ዓ.ም ናላ ፍውንዴሽን ። የመጀመሪያ ረቂቅ የካቲት 2013ዓ.ም

# ለአመቻቾች ማስታወሻዎች

## ምክሮች እና የጊዜ ሰሌዳ

ይህ መመሪያ (manual) ስለጤና እና ስለንፅህና አጠባበቅ ትምህርት ለማስተማር ጨዋታዎችን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል መመሪያ ይሰጣል ፡፡ የስልጠናው ክፍለ ጊዜያት በከፍተኛ ሁኔታ አሳታፊ ሊሆኑ እና ለተሳታፊዎች ተገቢውን የልምምድ ጊዜ መስጠት አለባቸው፤ ይሄም ተማሪዎች በእራሳቸው ት/ቤቶች የሚከናወኑትን ተግባራት እንዴት እንደሚጠቀሙ በራስ መተማመንን ይገነባሉ። በስልጠናዎች ወቅት ተሳታፊዎች ንቁ እንዲሆኑ ከጅመሩ አሰልጣኞች የሚጠበቅባውን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ስልጠናዎችን ከአካባቢያዊ ሁኔታ ጋር ማመቻቸት ትችላላችሁ፣ ነገር ግን ለልምምድ እና ለውይይት የሚሆን በቂ ጊዜ እንዳለ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በክፍለ-ጊዜው ውስጥ ተሳታፊዎች እንዲጠቀሙባቸው ተገቢውን የጨዋታ ቁሳቁሶች ብዛት ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

**ተሳታፊዎች፡** ይህ የሥልጠና ማኑዋል በወረዳ ደረጃም ሆነ በትምህርት ቤቶች አገልግሎት እንዲውል የተዘጋጀ ነው ፡፡ የፕሮግራሙ ሰራተኞች ስልጠናዎቹን እስከ ትምህርት ቤቶች ድረስ ሊያሰለጥኑ የሚችሉ የወረዳ ተወካዮችን ያሰለጥናሉ ፡፡ በዚህ ምክንያት የሁለቱም ደረጃ ሥልጠናዎች ከ1-5 ክፍለ ጊዜ ማካተት አለባቸው ፤ ስለሆነም ሁሉም ተሳታፊዎች ሌሎችን ከማሠልጠን ወይም ከማስተማራቸው በፊት ተግባራቱን የመለማመድ ዕድል ይኖራቸዋል ፡፡ ሆኖም ክፍለ ጊዜ 5 (ማቀድ) በታዳሚዎች ላይ ተመስርተው ሊስማሙ ይችላሉ፡፡ በትምህርት ቤቶች ውስጥ መምህራኑ ከሰለጠኑ የት/ቤቱ ተወካይ ሥልጠናውን ማግኘት አለባቸው፡፡

**ስልጠናውን ወደታች ማውረድ:** እቅዱ እንደሚከተለው ወደ ታች ይወርዳል፡

- የፕሮግራም ሰራተኞች ለወረዳ ተወካዮች- ከክፍለ ጊዜ 1-5
- የወረዳ ተወካዮች ለት/ቤት ተወካዮች - ከክፍለ ጊዜ 1-5
- የትምህርት ቤት ተወካዮች በስልጠናው ላልነበሩ - ከክፍለ ጊዜ 1-4
- የሰለጠኑ መመህራን ለተማሪዎች፡ - በመምህሩ መጽሐፍ ውስጥ ባለው ክፍለ ጊዜ

**የሥልጠና ዘዴ፡** አምስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እያንዳዱን ለማጠናቀቅ ከ1-2 ሰዓት ይወስዳል። የተጠቀሰው ሰዓት በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ይሰጣሉ ፡፡ ይህ የእያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜ መሰረታዊ መዋቅር ነው።

1. **መክፈቻ፡** ለመወያያ የተወሰኑ ጥያቄዎችን ወይም ቀልዶችን እንዲያቀርቡ በጥንድ በጥንድ እያደረጉ መጠየቅ ፡፡
2. **ቀጥተኛ መመሪያ:** መረጃውን ከተሳታፊዎች ጋር መከለስ ፡፡ ይህንን ክፍል በፎቶዎች እና በትምህርታዊ ገለፃ መደገፍ ይቻላል። ጥያቄዎች ለውይይት ተካተዋል ፡፡
3. **ክህሎት ተኮር** ፡ ክፍለ ጊዜ 1-4 የተወሰኑ የማስተማሪያ ክህሎቶችን የሚሸፍን ሲሆን የተሳታፊዎቹን የሙያ እድገት ለመደገፍ እና እንደ መምህር የሚጠበቅባቸውን የራስ የመተማመን ስሜት ለማሻሻል ይጠቅማል።

4. **እራሳቸውን ችለው መስራት:** ተሳታፊዎች ጨዋታዎቹን ለመለማመድ ፣ ለመወያየት ወይም ለማቀድ ጊዜ ይኖራቸዋል ፡፡ መመሪያዎቹን መረዳታቸውን ማረጋገጥ

**መርሃ-ግብር:** ለውይይት ፣ ለልምምድ እና እቅድ ለማቀድ ተጨማሪ ጊዜ ስለሚሰጥ የ 1.5 ቀን የስልጠና ፕሮግራም ይመከራል:

| በምክረ-ሀሳብ ደረጃ የቀረበ የሥልጠና ፕሮግራም | | |
|---|---|---|
| **ቀን** | **ሰዓት** | **ክፍለ ጊዜ** |
| ቀን 1 | 2:30- 4:30 | ✓ **የእንኳን ደህና መጣችሁ ለተሳታፊዎች**<br>✓ **ክፍለ ጊዜ 1:** ስለ ትራኮማ ማስተማር |
| | 4:30 - 4:45 | **የሻይ እረፍት** |
| | 4:45 - 6:30 | ✓ **ክፍለጊዜ : 2 በሽታን መከላከል እና የባህሪ ለውጥ ማምጣት** |
| | 6:30 - 7:30 | **የምሳ እረፍት** |
| | 7:30 - 9:15 | ✓ **ክፍለጊዜ : 3: ከለጅነት ጊዜ ጋር ለማያያዝ ተረቶችን መንገር**<br>✓ **የቀን 1 መዝጊያ** |
| ቀን 2 | 2:30 - 4:30 | ✓ **እንኳን በደህና መጣችሁ**<br>✓ **ክፍለ ጊዜ 4:** ለተነሳሽነት እና ግብ ለማስቀመጥ የሚሆኑ ጨዋታዎች፡፡ |
| | 4:30 - 4:45 | **የሻይ እረፍት** |
| | 4:45 - 6:30 | ✓ **ክፍለ ጊዜ 5:** እቅድ ማውጣት<br>✓ **የቀን 2 መዝጊያ** |

**የሥልጠና ቁሳቁሶች:** ቁሳቁሶችን ሲያሰራጩ ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ ፡፡ እነዚህ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ስለሆኑ እነዚህን የትምህርት ቤት ቁሳቁሶች ስልጠናው ካለቀ በኋላ እንዲያሰራጩ እንመክራለን፡፡

| የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች | | |
|---|---|---|
| **የቁሳቁሱ አይነት** | **ለሥልጠና የሚሆን ብዛት** | **ለትምህርት ቤቱ የሚሆን ብዛት** |
| እስክሪብቶች ፣ ወረቀት ፣ ትልቅ ተገላጭ ውረቀት (flipchart) ማርከር እና ፕላስተር | በአሰልጣኙ የሚወሰን | - |
| የሥልጠና መመሪያ(Manual) | ለእያንዳንዱ ተሳታፊ 1 | 1 በትምህርት ቤት |
| የአስተማሪው መጽሐፍ | ለእያንዳንዱ ተሳታፊ 1 | 2 በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት |
| የትግበራ መጽሐፍ (1-2 ኛ ክፍል) | ለ4 ተሳታፊዎች 1 መጽሐፍ | ~100 በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት (በትምህርት ቤት የተማሪዎች ቁጥር ተመስርቶ ይለያያል) |
| የቦርድ ጨዋታዎች + ካርዶች + የመጫወቻ ጠጠር (3-5 ኛ ክፍል) | ለ4 ተሳታፊዎች 1 | 3 በትምህርት ቤት ሁሉንም የጨዋታ ቁሳቁሶች ያካተተ |

| | | |
|---|---|---|
| ፈታኝ ሰንደቅ (Poster) (ጤና፣የወሃ እና የንፅህና አጠባበቅ) | ለ8ተሳታፊዎች 1 | 2 በትምህርት ቤት |
| ሜዳልያ /የደረት ባጅ | 1 በተግባር ለማሳየት | 2 (በትምህርት ቤቱ በኩል የሚቀርብ) |
| የእጅ መታጠቢያ አቃዎች (የመታጠቢያ ሳህን + ውሃ + ሳሙና + ንጹህ ፎጣ) | 1 በተግባር ለማሳየት | (በትምህርት ቤቱ በኩል የሚቀርብ ሆኖ ቁጥሩ በሰልጣኞች ይወሰናል) |
| ሳሙና | 1 በተግባር ለማሳየት | (በትምህርት ቤቱ በኩል የሚቀርብ ሆኖ ቁጥሩ በሰልጣኞች ይወሰናል) |

**ለኮቪድ19 ጥንቃቄ (ደህንነት):** ስልጠናውን ሲያቅዱ ሁሉንም የኮቪድ-19 (CVID-19) መመሪያዎች መከተል ያስፈልጋል፡፡ ስልጠናው ጥሩ የአየር ዝውውር ባለበት ክፍል ውስጥ መሆኑን እና ተሳታፊዎች በሁሉም ክፍለ ጊዜያት የእጅ ማጽጃ ኬሚካል መጠቀም ወይም እጅን በውሃ እና በሳሙና መታጠብ እንደሚችሉ ማረጋገ፡፡ የተሳታፊዎችን የሙቀት መጠን መለካት እና የበሽታው ምልክቶች ማሳየት/አለማሳየታቸውን ወደክፍል ከመግባታቸው በፊት ማረጋገጥ ፡፡ ተሳታፊዎች የአፍ እና የአፍንጫ ጭምብል መልበሳቸውን እና ተራርቀው መቀመጣቸውን ማረጋገጥ። ለቡድን ስራዎች፣ የስልጠናው ጊዜያት ሁሉ ከተመሳሳይ ቡድን አባላት ጋር እንዲሰሩ በማድረግ ከሌሎች ጋር ያላቸውን ንክኪ መቀነስ፡፡

■ መግቢያ

# በት/ቤት ውስጥ በጤና እና ሥነ-ንፅህና የባህሪ ለውጥ ለማምጣት የሚደረጉ ጨዋታዎች

*ተማሪዎችን ስለራሳቸው ጤንነት እንዴት ማነቃቃት እና እንዲሳተፉ ማድረግ ይቻላል?*

የዚህ መመሪያ አላማ በተማሪዎች መካከል ጥሩ ጤንነት እና ንፅህናን ለማሻሻል ትምህርት ቤቶች ትምህርታዊ ጨዋታዎችን ለመጠቀም የሚያስችል ማዕቀፍ መዘርጋት ነው። ጨዋታዎች በእረፍት ጊዜያቶች ለመዝናናት ብቻ ሳይሆን መምህራን ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ እና በትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ውስጥ ለማነሳሳት እና ለማሳተፍ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ አስፈላጊ መሳሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ጨዋታዎች የአቻ ለአቻ መማማርን፣ መመራመርን፣ መወዳደርን እና መተባበርን ያበረታታሉ። የዚህ የጤና ፕሮግራም ግብ ተማሪዎች ጤናማ ባህሪያትን ከመማር ባሻገር ጤናማ ባህሪያትን በጨዋታ እንዲለማመዱ እና ለሌሎች እንዲያሳትፉ ለማነሳሳት ነው።

**ጨዋታዎች ለጤንነት**: በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉት ጨዋታዎች እና ተግባራት የግል ንፅህና እና የአካባቢ ጽዳት ባለመኖሩ የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከል አስፈላጊ በሆኑ ባህሪያቶች ላይ ያተኩራሉ ። ዋናው ትኩረቱ አይነ-ስውርነትን ሊያስከትል የሚችለውን ትራኮማ መከላከል እንዲሁም የአንጀት ውስጥ ጥገኛ (በአፈር ንክኪ የሚተላለፉ) ትላትሎችን እና የብላህርዝያን ተጋላጭነት መቅነስ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉም በሽታዎች ዝቅተኛ የሆነ የውሃ አቅርቦት፣ የአካባቢ ጽዳትና የግል ንፅህና አጠባበቅ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች የሚከሰቱ ትኩረት የሚሹ በሽታች (NTDs) ናቸው።

በሽታዎችን ለማከም መድሃኒት አስፈላጊ ቢሆንም በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ውስጥ የንፅህና አጠባበቅ እና የአካባቢያ ጽዳት ላይ አስፈላጊውን ለውጥ ካላመጡ ሰዎች እንደገና በበሽታዎች ሊጠቁ ይችላሉ።

**ትኩረት የሚሹ ሐሩራማ በሽታዎች (NTDs):** ከዓለም ሕዝብ ውስጥ ቢያንስ አንድ አራተኛ የሚሆኑት ትኩረት በሚሹ ሐሩራማ በሽታዎች ይሠቃያሉ። እነዚህ በሽታዎች አብዛኛውን ጊዜ ለሞት የሚዳርጉ ባይሆኑም ለስቃይ፣ ለአይነ-ስውርነት፣ ለአካል ጉዳት፣ ለአካላዊና አዕምሮዊ ዕድገት ውስንነት ምክንያት ሊሆኑ በመቻላቸው፣ ይሄም ትምህርት የመማር ፍላጎት ላይ እና ሥራ የመስራት ችሎታ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል። እንደ እድል ሆኖ ትራኮማን፣ በአፈር ንክኪ የሚተላለፉ የአንጀት ትላትሎችን እና ብልሃርዚያን ለማከምም ሆነ ለመከላከል በተነጻጻሪ ብዙ ወጭ የማይጠይቅ እና ቀላል ነው። ለነዚህ ሶስት በሽታዎች ህክምናን ከንፅህና አጠባበቅ እና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ላይ ከሚደረጉ ቀላል ለውጦች ጋር አቀናጅቶ የበሽታንውን ኡደት እና ድህነትን መስበር ይችላል። ይህ መመሪያ የተዘጋጀው ትራኮማ ለተስፋፋባቸው ማህበረሰቦች ነው።

**ጤናማ ባህሪያቶች :-** እነዚህን በሽታዎች ለመከላከል የሚረዱ ጥቂት የሚሆኑ ቁልፍ ባሕርያት አሉ ። ይህ መመሪያ ለትምህርት ቤት ተማሪዎች በሚከተሉት አምስት ቁልፍ መልእክቶች ላይ ያተኩረ ነው:

| ቁልፍ መልዕክት | የግል ባህሪዎች |
| --- | --- |
| **ንጹህ እጆች** | እጆቻችን በሳሙናና በውሃ መታጠብ |

| | |
|---|---|
| **ንጹህ ፊት** | ፊትን በሳሙና እና በውሃ ታጠብ። የፊት ማዳረቂያ ጨርቆች በጋራ አለመጠቀም |
| **ንጹህ አከባቢ** | መጸዳጃ ቤት መጠቀም፤ ሜዳ ላይም ሆነ በውሃ መገኛዎች አካባቢ አለመፀዳዳት |
| **ንጹህ ስፍራ** | መጸዳጃ በቶችን ፣ ክፍሎችን፣ እና ግቢን ማጽዳት |
| **ጤናማ የሆኑ ጓደኞች እና ቤተሰብ** | ጤናማ መልዕክቶችን ለሌሎች መንገር! |

**የማስተማሪያ ዘዴ:** ትምህርት ቤቶች ብዙውን ጊዜ በዋናነት በእውቀት ማስጨበጥ ላይ ያተኩራሉ፤ ነገር ግን ይህ የጤና ፕሮግራም የሰዎችን ባህሪ መለወጥ ይፈልጋል። የባህሪ ለውጥ ከግንዛቤ በላይ የሆነ ነገር እንዲመጣ የሚጠይቅ ሂደት ነው። በዚህ ምክንያት፣ ይህ የጤና ፕሮግራም በተማሪዎች መካከል የባህሪ ለውጥ ለማነሳሳት ተሳትፎን መሰረት ያደርገ የጨዋታ ዘዴን ይጠቀማል። ፕሮግራሙ ህፃናትን ስለበሽታ መከላከል ለማስገንዘብ የሚያዝናኑ እና ትርጉም የሚሰጡ ልምዶችን የማስተማሪያ ዘዴዎች አድረጎ አቅርቧል፡፡

ዓላማውም የሚከተሉትን ለማሳካት ነው:

- ✓ ***ከባህሪያት ጋር ስሜታዊ ትስስር መገንባት*** - ስለ አንድ በሽታ ማወቅ ለውጥ እንዲመጣ ለማነሳሳት ሁልጊዜ በቂ አይደለም። በዚህ ምክንያት፣ ትናንሽ ልጆች የበሽታውን ሁሉንም ዝርዝሮች በደንብ መገንዘብ አያስፈልጋቸውም፤ ይልቁንስ ከሚፈለገው ባህሪ ጋር ስሜታዊ ትስስር ከፈጠሩ የባህሪ ለውጥ የማምጣት ዕድላቸው ሰፊ ነው ፡፡ ፕሮግራሙ ታሪኮችን በመጠቀም የሰውን ችግር እንደራስ ማየትን የሚያበረታቱ ለህጻናት የታቀዱ ተግባራትን እና የተፈለገውን ባህሪ ከማድረግ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የአቻ ለአቻነት ስሜት ይጠቀማል ፡፡
- ✓ ***በንቃት እንዲማሩ በማድረግ ማነሳሳት:*** *በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ልጆቹ የአስተማሪውን መመሪያ ከመከተል በላይ ተግባራን ያከናውናሉ፤ እንዲሁም በተግባራት ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ፡፡ በጨዋታዎቹ ውስጥ፣ ባህሪያቸውን ለመለማመድ የሚያስችል፣ ግቦችን ለማውጣት እና የአቻዎቻቸውን ግብረ-መልሶች ለመቀበል አስደሳች፣ ያልተለመደ እና የማይሰለቹት አከባቢ ይፈጥርላቸዋል፡፡* መረጃውን በነፃነት በመመርመር ባህሪያትን በጨዋታ መልክ መሞከር ይችላሉ።
- ✓ ***ተማሪዎች አቻዎቻቸውን መምከር እንዲችሉ እና የጤና መልዕክተኛ እንዲሆኑ ማብቃት፦*** ሌላው ቀርቶ ትናንሽ ልጆች እንኳን አንድን ታሪክ መንገር እና የጤና መልዕክቶችን ለጓደኞቻቸው እና ለቤተሰቦቻቸው ማስተላለፍ ይችላሉ ፡፡ ትልልቅ ልጆች በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ጤናን መጠበቅ እና ንፅህና ማሻሻልን የሚያበረታቱ ተግባራትን መምራት ይችላሉ ፡፡ ለልጆች ሀላፊነት በመስጠት በራሳቸው ጤና ላይ የበለጠ የባለቤትነት ስሜት ማግኘት እና በአካባቢያቸው ያሉትን ሁኔታዎች በንቃት እንዲሻሻሉ ማድረግ ይችላሉ፡፡ በትምህርት ቤት እና በቤታቸው ውስጥ የባህሪ ለውጥ እየተደረገ መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው።

ቀለል ያሉ የዕለት ተዕለት ልምዶችን (ባህሪያትን) መለወጥ በበሽታ የመያዝን አጋጣሚ በእጅጉ ሊቀንስና ልጆችን እና ቤተሰቦቻቸውን ከአደጋ ሊጠብቅ ይችላል ፡፡ ፕሮግራሙ አስደሳችና ትርጉም ያለው ተሞክሮ በማሳለፍ ልጆችን ስለ በሽታ መከላከል ለማስተማር የሚረዱ ዘዴዎችን ይዟል ። አሰሳ እና ፈጠራን ማበረታታት በዚህ ፕሮግራም የሚመከሩ ዘዴዎች ናቸው። ይህም የልጆችን የግል ብቃት እና ኃላፊነት ስሜት ይጨምራል።

**የአስተማሪዎች ልዩ ሚና:** መምህራን በልጆች ትምህርት እና ማህበራዊ እድገት ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። ስለሆነም የትምህርት ቤት ሰራተኞችን ከጤና ጋር በተያያዙ ርዕሶች ላይ ማሠልጠን እና እንደ አርአያነት የሚያስችሏቸውን እና ከልጆች ጋር

በሚያደርጉት ሥራ ሊረዷቸው የሚችሉ ክህሎቶችን ማሟላት አስፈላጊ ነው፡፡ በልጆች ትምህርት ውስጥ ባላቸው ወሳኝ ሚና ምክንያት መምህራን ለፕሮግራሙ ስኬት ብዙ ኃላፊነት አለባቸው ፡፡

መምህራን ተማሪዎቻቸውን በተሻለ ስለሚያውቁ የተማሪዎቻቸውን ፍላጎቶች እና የአካባቢያዊ ሁኔታን በተሻለ ሁኔታ ለማመቻቸት የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎችን ማመቻቸት አለባቸው ፡፡ መምህራኑ እና የክበብ አስተባባሪዎች የጤና ፕሮግራሙን በትምህርት ቤቶቻቸው እና በተማሪዎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ለውጥ ለማምጣት ፣ ጤናማ ባህሪያትን ለማበረታታት እና የበሽታ ተጋላጭነታቸውን ለመቀነስ ይችላሉ። እንዲሁም መምህራን በየቀኑ ተማሪዎቻቸውን ስለሚያዩ፥ የፕሮግራሙን ለውጥ ለመከታተል እና ልጆች በባህሪያቸው በአዎንታዊ ለውጦች ላይ እንዲቀጥሉ ማበረታታት ይችላሉ ፡፡

**ማስታወሻዎች:** በፕሮግራሙ ይዝናኑ!! ግቡ ትልቅ ቢሆንም (በሽታን መቀነስ እና የህፃናትን ጤና ማሻሻል)፣ አገልግሎቱ ለሁሉም (መምህራን እና ተማሪዎች) አዝናኝ መሆን አለበት ፡፡

# ክፍል 1፡ ስለ ትራኮማ ማስተማር

## 1.1 የመክፈቻ ጥያቄዎች

*ጊዜ: 10 ደቂቃዎች*

*ጥንድ ጥንድ እየሆኑ በጥያቄዎቻቸው ላይ አብረው እንዲወያዩ 5 ደቂቃ ስጣቸው። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ሁሉንም ሰው አንድ ላይ ሰብስበህ ሁሉንም ጥያቄዎች ጠይቅ ። መልሶችቻቸውን በሰፊ ወረቀት ላይ (flip chart ) ፃፋቸው ወይም ተሳታፊዎች እርስበርሳቸው ምላሽ እንዲሰጡ መጠየቅ ይችላሉ ።*

- **ለጥንዶች፡** በትምህርት ቤት ባሳለፋችሁት ዓመታት የምትወዱት አስተማሪ ማን ነበር? ይህ አስተማሪ ጥሩ አስተማሪ እንዲሆን ያስቻለው የተለየ ባሕርይ ምንድን ነው?
- **ለሁሉም ቡድን፡** ውጤታማ አስተማሪ እንዲሆን የሚያደርጉት ባሕርያት የትኞቹ ናቸው? ተማሪዎች እንዲማሩ የሚያነሳሱባቸው ጥሩ ጥሩ መንገዶች ምንድን ናቸው?

## 1.2 ስለፕሮግራሙ መግቢያ

*15 ደቂቃዎች*

*ፕሮግራሙን ለተሳታፊዎች አስተዋውቁ*

ይህ ማህበረሰብ ለጤና ትምህርት ፕሮግራም የተመረጠው ዓይነ-ስውርነት የሚያስከትለውን የትራኮማ በሽታ በስፋት ስለሚከሰት ነው። ትራኮማ በትንንሽ ልጆችና እነሱን በሚንከባከቧቸው ሴቶች ዘንድ በጣም የተለመደ ነው። ህክምና ካልተደረገለት እና ካልተከላከልነው ይህ በሽታ የዕድሜ ልክ የአካል ጉዳት እና ችግር ሊያስከትል ይችላል። ደግነቱ በባህሪያችን ላይ ቀላል የሆነ ጤናማ ለውጥ በማድረግ ትራኮማ እንዳይከሰት ማድረግ በጣም ቀላል ነው። እነዚህ ጤናማ ልማዶች በበሽታ የመያዝን አጋጣሚ በእጅጉ ሊቀንሱና ልጆችንም ሆነ ቤተሰቦቻቸውን ከትራኮማና ከሌሎች ከንጽሕና ጋር ተያያዥነት ያላቸው በሽታዎች ሊከላከሉ ይችላሉ።

**ግብ፡-** ፕሮግራሙ በልጆች ባሕርይ ላይ ተጽዕኖ ለማሳደርና በትምህርት ቤቶችም ሆነ በቤት ውስጥ ጤናማ የንጽሕና አጠባበቅ ልማድ እንዲፈጥሩ ለማድረግ ነው።

*<u>ተሳታፊዎች እጃቸውን እያነሱ መልሳቸውን እንዲሰጡ ንገሯቸው:</u> ለ ኮቪድ-19 (COVID-19) ሰዎች በአደባባይ የአፍ እና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል እንዲለብሱ ተነግሯቸው ነበር። በአሁኑ ጊዜ በአናንተ ማህበረሰብ ውስጥ ምንያህል ሰዎች የአፍ እና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ያደርጋሉ?*

- *አብዛኞቹ ሰዎች?*
- *ግማሽ ያህሉ ሰዎች?*
- *ማንም የለም ማለት ይቻላል?*

**ዘዴዎች፡** ኮቪድን ለመከላከል ጭምብል (mask) ማድረግ የባህሪ ለውጥ ምሳሌ ነው **፡፡** ሰዎች ጭምብል ማድረግ እንዳለባቸው ቢያውቁም በርካታ ሰዎች ግን ይህን ማድረግ አልቻሉም ። የባህሪ ለውጥ ማመጣት ከእውቀት በላይ የሆኑ ነገሮችን ይጠይቃል፤ ተነሳሽነት ፣ የአቻ ግፊት እና ከለውጡ ጋር ስሜታዊ ትስስር ይፈልጋል። የጤና ፕሮግራሙ የህፃናት ተማሪዎችን ተሳትፎ ለማግኘት እና በልጆች የለውጥ ተነሳሽነት እንዲኖር ለማድረግ ጨዋታዎችን እና ሌሎች ዘዴዎችን ይጠቀማሉ ፡፡ ጨዋታዎች በእረፍት ጊዜ መዝናኛ ብቻ ሳይሆኑ በክፍል ውስጥ የሚሰጥ ጠቃሚ እና መደበኛ የትምህርት አካል መሆን ይችላሉ ፡፡

**ስለ ስልጠናው:** መምህራን በክፍል ውስጥ ያሉትን እንቅስቃሴዎች እንዲጠቀሙ ለማዘጋጀት፤ ሥልጠናው ለአስተማሪዎች ይበልጥ አሳታፊ አቀራረቦች ላይ የሙያ ክህሎቶችን ማጎልበትንም ያካትታል ፡፡ በተጨማሪም ፣ እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ለተሳታፊዎች ክህሎቶችን እና ተግባራትን ለመለማመድ እድል ስለሚሰጥ ከጊዜ በኋላ እነዚህን ችሎታዎች መጠቀም ይበልጥ ቀላል እንዲሆንላቸው ያደርጋሉ።

**ስለ ጨዋታዎቹ:** በስልጠናው ወቅት ለትምህርት ቤቶቹ የሚተዋወቁና ልምምድ የሚደረግባቸው ሶስት ተግባራት አሉ። የመጀመሪያው ከ1-2 ኛ ክፍል ለሚሆኑ የትግበራ መፅሐፍ ነው። ንፅህናን ለማስተማር ተረት መሳሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ትኩረት ይሰጣል። ከ3-5ኛ ክፍል ላሉት አወዳዳሪ የቦርድ ጨዋታ አለ ፤ እንዲሁም የጤና እና የዋሽ ከበባት በፈታኝ ጨዋታ እርስ በእርስ ይወዳደራሉ ፡፡ ወደ መጨረሻ ባሉት ክፍለ-ጊዜያት እነዚህ ጨዋታዎች ተብራርተው ይቀርባሉ እንዲሁም ለልምምድ ጊዜ ይኖራል ፡፡

## 1.3 ስለ ትራኮማ አጭር ማጠቃለያ

*20 ደቂቃዎች*

*መረጃውን ከተሳታፊዎች ጋር መገምገም ፡፡ ይህንን ክፍል በፎቶዎች ፣ በትምህርታዊ ገለፃ ወይም በውይይት ማሟላት ይችላል ፡፡*

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የትራኮማ ጫና ያለባት ሀገር ናት፤ ከ657 ወረዳዎች በላይ ትራኮማ የሚታይባቸው ሲሆን ወደ 75 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች ደግሞ ለበሽታው ተጋላጭ ናቸው። ትራኮማ በዓለም ላይ ዋነኛ የዓይነ-ስውርነት መንስኤ በመሆኑ እነዚህ ቁጥሮች በጣም ያሳስባሉ።

*መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል:- በትምህርት ቤትህ (ወይም በወረዳህ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች) ተማሪዎች ከትራኮማ ወይም ከሌሎች በሽታዎች ጤናማ ሆነው እንዲቀጥሉ የሚረዱ ፕሮግራሞች አሏቸው? ምን ዓይነት እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ?*


**ትራኮማ፡-** ትራኮማ የሚከሰተው ክላሚዲያ ትራኮማቲስ በተባለ የባክቴሪያ ዝርያ አማካኝነት ነው፤ ባክቴሪያው በበሽታው ከተያዘ ሰው አፍንጫና የዓይን ፈሳሽ ጋር በመገናኘት፣ አይን አካባቢ ማረፍ በሚወዱ ዝንቦች፣ አይን አካባቢን በእጅ በመነካካትና የፊት ፎጣ በጋራ በመጠቀም ይተላለፋል። በሽታው አብዛኛውን ጊዜ በቂ የንጽሕናና የንጹህ ውሃ እጥረት በሚኖርባቸው የገጠር ማህበረሰቦች ውስጥ በብዛት ተስፋፍቶ ይገኛል።

**ተጋላጭ ቡድኖች:** ጤናማ ባልሆነ የንፅህና አጠባበቅ ልምዶች ምክንያት ልጆች (ከ1-9 ዓመት ዕድሜ ያላቸው) በተለየ መልኩ ለትራኮማ በሽታ ተጋላጭ ናቸው ፡፡ ይሁን እንጂ በሽታው ቀስ በቀስ ስለሚያድግ እስከ ጎልማሳነት እሜቸው ድረስ ከፍተኛ የህመም ስሜት እና ዘላቂ የሆነ ጉዳት ላያሳዩ ይችላሉ። ሴቶች አራት እጅ ከወንዶች በበለጠ በትራኮማ አማካኝነት ለሚመጣው አይነ-ስውርነት ተጋላጭ ናቸው፤ ይሄም የሆነው በልጅነታቸው ተጋላጭ ስለሆኑ እና ትልቅ ከሆኑ በኋላም ልጆችን በመንከባከብ እንዲሁም አብዛኛውን ጊዜ የጽዳት ስራ የሚሰሩት ሴቶች ስለሆኑ ተጋላጭ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው፡፡

**የበሽታው ምልክቶች፡-** ትራኮማ አብዛኛውን ጊዜ በሁለቱም ዓይኖች ላይ ጉዳት የሚያደርስ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ የበሽታው ምልክቶች ከላይኛው የአይን ሽፋን ላይ ይበልጥ ከባድ ናቸው። በትራኮማ በሽታ የተያዘ ሰው ብዙውን ጊዜ የሚከተሉትን የበሽታው ምልክቶች ይታዩበታል፡-

- የዐይን ቆብ መቆጣት እና የማቃጠል ስሜት
- ንፍጥ መሳይ ወይም መግል የያዘ ፈሳሽ ከአይን መውጣት
- የብርሃን መፍራት/ለማየት መቸገር
- የአይን የህመም ስሜት
- ደብዛዛ እይታ
- የዐይን ሽፋሽፍት ወደውስጥ መቀልበስ (በሽታው ከፍተኛ ደረጃ ከደረሰ)

  አንድ ሰው በልጅነት ዕድሜው በተደጋጋሚ በበሽታው ከተያዘ የአይኑ ሽፋሽፍት ወደ ውስጥ በመቀልበስ አይኑን በሚያርገበግብበት ጊዜ የአይን መስታውቱን/ብሌንን ይፍቀዋል። ይህ ደግሞ ጠባሳ በመፍጠር፣ የማየት ችሎታን እያዳከመ በጊዜ ሂደት ዓይነ-ስውር እንዲሆን ያደርገዋል።

| የትራኮማ በሽታ ደረጃዎች | | | |
|---|---|---|---|
|  |  |  |  |
| ጤናማ ዓይን | ዓይንን የማቃጠል ስሜት እና ፍሳሽ መውጣት | የዐይን ቆብ እብጠት | የዐይን ሽፋሽፍት ወደ ውስጥ በመታጠፍ የአይን መስታውትን/ብሌን ይፍቀዋል (ወደ ዓይነ-ስውርነት የሚያመራ ከፍ ወዳለ ደረጃ የሚደረስ በሽታ ነው) |

**መተላለፊያ፡-** ትራኮማ ተላላፊ በሽታ ነው፤ መተላለፊያውም በሽታው ከተያዘ ሰው ዓይን ወይም አፍንጫ ከሚወጣው ፈሳሽ ጋር በተለያዩ መንገዶች ንክኪ ሲኖር ነው። ንፅህና የጎደለው ፊትና ንፅህናው ያልተጠበቀ አካባቢ (ሜዳ ላይ መጸዳዳት) ለትራኮማ በሽታ መተላለያ ምቹ ሁኔታ ሆኖ ያገለግላል።

*መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል፡-* *ትራኮማ በትምህርት ቤቶች ለህጻናት አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያደርገው በምን አይነት መንገድ ነው? ይህ የኀለበተ በሽታ የሰዎችን ሕይወት ይበልጥ አስቸጋሪ ሊያደርገው የሚችለው እንዴት ነው?*

አምስቱ ዋና ዋና የትራኮማ በሽታ መተላለፊያ መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፡

- **ሰገራ** ፡ሰገራ ዝንቦችን በቀላሉ በመሳብ ለዝንቦች ምቹ የመራቢያ ቦታ ይፈጥራል፡፡ በመኖሪያ አካባቢዎች ወይም በትምህርት ቤቶች አቅራቢያ ሰገራ መኖሩ በበሽታው የመያዝ እድልን ከፍ ያደርጋል።
- **ፊት፡** ከአፍንጫ እና ከአይን የሚወጣ ፈሳሽ ወደ ሌሎች ግለሰቦች ሊተላለፍ የሚችል ባክቴሪያን ይይዛል፡፡

- **ዝንቦች** : "አይን ላይ ማረፍ የሚወዱ ዝንቦች" በበሽታው ከተጠቃው ሰው ፊት ፈሳሽ ላይ ባክቴሪያን በመሸከም ወደ ጤነኛው ሰው ያስተላልፋሉ፤ ይህም በሺታውን ያሰራጨዋል።
- **ልብሶች (ጨርቆች)**: በበሽታው በተጠቁ እና ጤናማ በሆኑ ሰዎች መካከል ፎጣዎችን/ ጨርቆችን መጋራት ባክቴሪያውን ወደ ጤናኛው ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡
- **እጆች**: የተበከለውን ዐይን በጣቶች ከነኩበኋላ ከሌላ ግለሰብ ጋር መነካካት (ለምሳሌ እጅ መጨባበጥ) በሺታውን ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

በክፍል 2፣ በተወሰኑ ትራኮማን የሚከላከሉ ባህሪያት ላይ ውይይት እናደርጋልን፡፡ አሁን ለሌሎች ማስተማር ስለምትችሏቸው የተለያዩ መንገዶች እንወያያለን፡፡

## 1.4 ትኩረት: የማስተማሪያ ዘዴዎች (style)

*15 ደቂቃዎች*

*መረጃውን ከተሳታፊዎች ጋር መገምገም ፡:*

**መምህር-ተኮር:** በተለምዶ፣ አብዛኛው ትምህርት በመምህሩ ዙሪያ ያተኮረ ነበር፡፡ በመምህር-ተኮር አካሄድ አስተማሪው በቀጥታ በሚሰጠው መመሪያ እና ትምህርታዊ መግለጫ ላይ በመመርኮዝ ተማሪዎቹ የሚማሯቸውን ሁሉንም ዕውቀቶች በበላይነት ይመራል፡፡ አስተማሪዎቻቸውን ማዳመጥ እና መረጃን መውሰድ የሚፈልጉ ተማሪዎች ሁሉንም እንደሚቀበል እንደ "ነጭ ወረቀት" ይቆጠራሉ። ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ጥያቄዎችን ሊመልሱ ወይም መልመጃዎችን ሰርተው ሊጨርሱ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ይሄን የሚያደርጉት ለአስተማሪው መመሪያ ምላሽ ብቻ ነው።

- ✓ **ለምን አይነት ሁኔታ ይመከራል:** እጅግ በጣም ትላልቅ ለሆኑ ክፍሎች፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው ይዘት ለማስተማር፤ አንድ የተወሰነ ዘዴ ለማስተማር (ሳይንስ ፣ ሂሳብ)
- × **ድክመቶች:** ተማሪዎችን የሚያነቃቃ ወይም አሳታፊ አይደለም፤ ትናንሽ ልጆች ትኩረት የመስጠት ችግር ሊገጥማቸው ይችላል፤ ተማሪዎች ከይዘቱ ጋር የተስማማ የስሜት ግንኙነት ላይኖራቸው ይችላል።

**ተማሪን ማዕከል ያደረገ (ተማሪ-ተኮር):** በቅርብ አስርት ዓመታት ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ አቀራረብ የበለጠ ትኩረት አግኝቷል ፡፡ በዚህ አካሄድ ተማሪዎቹ በዝምታ የሚያዳምጡ ብቻ አይደሉም፤ ይልቁንስ በአስተማሪው መሪነት የራሳቸውን ትምህርት በንቃት ይማራሉ። አስተማሪው በዚህ ዘዴም ቢሆን በክፍል ውስጥ የመምራት ሥልጣኑ የእርሱ ነው፣ ነገር ግን እርሱ ሙሉውን ክፍል በብቸኝነት አይዝም። ይልቁንም መምህሩ እንደ አስተባባሪ ሆኖ ተማሪዎችን በእንቅስቃሴዎች፣ በአሰሳ እና አቻ ለአቻ ትምህርት እንዲማሩ የሚያስችል ማዕቀፍ ይሰጣል፡፡ ይህ አካሄድ ተማሪዎቹ ችሎታን እንዲያዳብሩ፣ ችግሮችን እንዲፈቱ እና ለስኬታቸው በባለቤትነት እንዲወስኑ ያስችላቸዋል።

- ✓ **ለምን አይነት ሁኔታ ይመከራል:** የማስተማር ክህሎትን; ችግር ፈችነትን እና ፈጠራን ማበረታታት፤ የባህሪ ለውጥን ማነሳሳት፤ ጥልቀት ያለው አስተሳሰብን እና ራስን መግለጽን ማዳበር።
- × **ድክመቶች:** ከፍተኛ መጠን ያለው ይዘት ለመሸፈን አስቸጋሪ መሆን፤ ዝምተኛና ዝቅተኛ ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎች ሁሉንም በተሳትፎ የሚገኙ ጥቅሞች ላያገኙ ይችላሉ።

*<u>መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል:</u> በማህበረሰባችሁ ውስጥ ምን ዓይነት የማስተማር ዘዴ ነው የተለመደው? በክፍል ውስጥ በተማሪዎች የሚመሩ ተግባራት አሉ?*

በሁለቱም አይነት አቀራረቦች ጥቅሞች እና ጉዳቶች ምክንያት፣ አብዛኛዎቹ መምህራን የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በማጣመር ትምህርት አሰጣጣቸውም እንዲሁ ይለያያሉ:: በእርግጥ ይህ የሥልጠና መመሪያ መምህር-ተኮር እና ተማሪ-ተኮር ክፍሎችን ያካተተ ሲሆን እንደ ድብልቅ ዘዴ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል::

የሚከተለው ሰንጠረዥ አምስት የማስተማሪያ ዘይቤዎችን ገፅታዎች ከብዙ መምህር-ተኮር እስከ ብዙ ተማሪ-ተኮር ድረስ ያሳያል ::

| | **መምህር-ተኮር ⬅ ወደ ➡ ተማሪ-ተኮር** | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **ዘይቤ** | ትምህርታዊ ገለፃ / የመምራን ስልጣን | **በተግባር ማሳየት/ አሰልጣኝ ዘይቤ** | ቅልቀል /ድብልቅ | አመቻች / በተሳታፊው የመንቀሳቀስ ዘይቤ | ወኪል / ቡድን |
| **የአስተማሪ ሚና** | መንገር | በተግባር ማሳየት | ድብልቅ | መምራት | ማማከር |
| **የተማሪዎች ሚና** | መስማት፤ማስታወሻዎችን መውሰድ | መመልከት፤መመሪያዎችን መከተል | ድብልቅ | መሳተፍ፤አዳዲስ ነገሮችን ማሰስ | መተባበር፤ ማነሳሳት |
| **ምሳሌዎች** | ሌክቸር፣ ትምህርታዊ ገለፃዎች | ሰርቶ ማሳያ ፤ አስተማሪ ሞዴሎችን ያሳያል እንዲሁም ተማሪዎች ምሳሌውን ይከተላሉ | ድብልቅ | ጨዋታዎች፤ ጭውውት፤ ውይይት | የቡድን ሥራ፤ ፕሮጀክቶች |

አንዳንድ ጊዜ መምህራን በክፍል ውስጥ በአብኛው ተማሪ-ተኮር የሆነ አቀራረብን መጠቀም ምቾት አይሰማቸውም:: ይሄም ያላቸውን ቁጥጥር እንደሚያዳክም ወይም ክፍለ-ጊዜው እንደሚዘገይባቸው ስለሚሰማቸው ነው:: ሆኖም ፣ አንድ አስተማሪ በክፍሉ ማዕከል ውስጥ ሳይኖርም የክፍሉ ሐላፊ ገፀ-ባህሪ ሊኖረው ይችላል። እንዲሁም ተማሪዎቹ በትምህርታቸው የበለጠ ይሳተፋሉ በተጨማሪም ብዙውን ጊዜ ከተማሪ-ተኮር ተግባራት የተሻለ ዕውቀቱን ይይዛሉ ፣ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ስኬታማ እንዲሆኑ የሚረዳቸውን ክህሎቶች ያገኛሉ። የዚህ የጤና ፕሮግራም ግብ እውቀትን ከማግኘትም በላይ ጤናማ የባህሪ ለውጦችን ስለሚያነሳሳ የተማሪ-ተኮር እንቅስቃሴዎችን (ጨዋታዎችን) አጠቃቀም እናበረታታለን ::

*መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል፡- በክፍል ውስጥ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መጠቀም የሚያስጨንቀውን አስተማሪ እንዴት ልታሳምነው ትችላለህ?*

## 1.5 ተግባር: ጭውውት

*40 ደቂቃዎች*

*የሚከተሉትን መመሪያዎች ከተሳታፊዎች ጋር በጋራ በመሄድ በቡድን እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ አካሄዳቸውን ለመከታተል እና ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት በክፍሉ ውስጥ መንቀሳቀስ ትችላለህ፣ በክፍል ውስጥ ተሳታፊዎች በንቃት እንዲሰሩ አድርግ፡፡*

ክፍለ ጊዜ አንድን ለማጠናቀቅ፣ ተሳታፊዎች የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ለመገምገም እና የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመለማመድ ጭውውት ያደርጋሉ፡፡

*የጭውውቱ መመሪያ:*

1. ተሳታፊዎች ከ4-8 ሰዎች በመሆን ቡድን እንዲሰሩ መንገር።
2. የትራኮማ መተላለፊያ መንገዶችን (አምስት ዋና ዋና መንገዶች) ለማስተማር ጭውውት እንዲሰሩ መንገር። አንድ ሰው “አስተማሪ” ሁኖ ጭውውት ሲሰራ ሌሎች ተሳታፊዎች ደግሞ “ተማሪ” ሁነው ጭውውቱን ይሰራሉ፡፡ በጭውውቱ ወቅት ሚናቸውን መቀየር ይችላሉ ፡፡
3. በመጀመሪያ ተሳታፊዎች በትራኮማ መተላለፊያ መንገድ ላይ መምህር-ተኮር ትምህርት ላይ ጭውውት ያደርጋሉ፡፡ አስተማሪው በዚህ ጭውውት ውስጥ ሁሉንም ንግግሮች ማለት ይኖርበታል። ይህን ጭውውት ለመለማመድ 10 ደቂቃ ይሰጣቸዋል።
4. ቀጥሎ በትራኮማ መተላለፊያ መንገድ ላይ ተማሪ-ተኮር ትምህርት ላይ ጭውውት ያደረጋሉ፡፡ ተማሪዎቹ በዚህ ጭውውት ውስጥ አብዛኛውን ንግግር ማድረግ አለባቸው፡፡ በቡድን ሥራ ፣ በድራማ ፣ እርስ በእርስ በመማማር ወይም ጨዋታ በመጫወት መማር ይችላሉ፡፡ መምህሩ ተማሪዎችን መመሪያዎችን በማሳየት ይረዳል ነገር ግን ተማሪዎቹ እንዲመሩ ያደርጋቸዋል ፡፡ ይህን ጭውውት ለመለማመድ 10 ደቂቃ ይሰጣቸዋል።
5. ቡድኖቹ ልምምድ በሚያደርጉበት ወቅት ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እና የተሻለ መስራታቸውን ለመከታተል በክፍሉ ውስጥ መንቀሳቀስ፡፡
6. ሁሉም ቡድኖች ጭውውቱን ለመለማመድ ጊዜ ካገኙ በኋላ 2 ቡድኖች ወደ ፊት መጥተው የየራሳቸውን ጭውውት ለሁሉም እንዲያቀርቡ መጠየቅ፡፡
7. *ጥያቄ*
   - ለተማሪዎች ይበልጥ አሳታፊው ዘዴ የትኛው ነው?
   - የትኛውን ዘዴ ትመርጣላችሁ? ለምን? ወይስ ይህን ትምህርት ለማስተማር ሌላ የምትመርጡት ዘዴ አለ?

■ ሁሉም አስተማሪዎች እና አሰልጣኞች

# ክፍል 2፡ በሽታን መከላከልና የባህሪ ለውጥ ማምጣት

## 2.1 “ቀልድ” ማዘጋጀት

*15 ደቂቃዎች*

*አመቻቹ ተሳታፊዎች ለተወሰኑ ንግግሮች ምላሽ ለመስጠት የሚቆሙበት ወይም የሚቀመጡበት መልመጃዎች እንዲሰሩ ይመራቸዋል፡፡.*

ባለፈው ክፍለ-ጊዜ ሰዎች መረጃን ማስተማር ስለሚችሉባቸው የተለያዩ መንገዶች ተወያይተናል ፡፡ ሆኖም ፣ ሰዎች በተለያዩ መንገዶች መማር እንደሚችሉም መገንዘብም አስፈላጊ ነው ፡፡ ተማሪዎችን ስለ ትራኮማ በምናስተምርበት ወቅት ተማሪዎች በሚያስታውሱት እና በውስጣቸው እንዲቅር በሚያደርግ መንገድ እንዲማሩ እንፈልጋለን ፡፡ እኛም ራሳችን እንደተማሪ ሆነን በማሰብ ይህንን ክፍለ ጊዜ እንጀምራለን፡፡ እንዴት በተሻለ መንገድ እንማራለን?

*<u>ቀልዶችን ለማቅረብ መመሪያዎች</u>*

1. አሰልጣኙ ስለሆነ ነገር ንግግር ያደርጋል።
2. ተሳታፊዎች ንግግሩ ለእነርሱ እውነት ከሆነ ይቆማሉ። ካልሆነ እንደተቀመጡ ይቀራሉ።
3. አሰልጣኙ ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጡ ተሳታፊዎችን ሊጠራ ይችላል።

*ንግግሮች/የሚቀርቡ ሐሳቦች:*

- ማንበብ የሚያስደስታችሁ እና የሚያዝናናችሁ ከሆነ ቁሙ (ይሄም ለሥራ ሳይሆን) ።
- ጥሩ አቅጣጫን የማወቅ ስሜት ያላችሁ እና በአዳዲስ ቦታዎች ላይ መንገዳችሁን በቀላሉ ማግኘት የምትችሉ ቁሙ ፡፡
- ሂሳብ ወይም ቁጥራዊ መረጃ ከምትወዷቸው የትምህርት ዘርፎች ውስጥ ከሆነ ቆሙ ፡፡
- ሥዕል መሳል የምትውዱ እና ጎበዝ እንደሆናችሁ የምታስቡ ቁሙ ፡፡
- ታሪኮችን (ተረት) መናገር የምትውዱ ከሆነ ቁሙ።
- ብቻህን ስትሆን የተሻለ የምትሰራ ከሆነ ቁም ፡፡
- በቡድን እና ከሌሎች ሰዎች ጋር በተሻለ ሁኔታ የምትሰሩ ከሆነ ቁሙ ፡፡
- የመዝሙሮችን ቅላፄዎች እና ዜማዎችን በቀላሉ ማስታወስ የምትችሉ ከሆነ ቆሙ ፡፡
- በስፖርቶች መዝናናት የምትወዱ ከሆነ ቁሙ።
- ተፈጥሮን በማድነቅ ጊዜ ማሳለፍ የምትወዱ እና ብዙ የተለያዩ የእጽዋት እና የእንስሳት ዓይነቶችን መለየት የምትችሉ ከሆነ ቁሙ ፡፡

*ውይይቱን ለማስቀጠል የሚነሱ ጥያቄዎች፡-*

- አብዛኞቹ ሰዎች በትኛው ሐሳብ ቆሙ?
- ቡድኑ በሳይንቲስቶች ወይም በፖሊሶች የተሞላ ቢሆን ኖሮ መልሱ ከዚህ የተለየ ይሆናል ብላችሁ ታስባላችሁ?


## 2.2 የ“ማመንን” ስልት

15 minutes

*መረጃውን ከተሳታፊዎቹ ጋር መገምገም። ይህን ክፍል በፎቶ፣ በትምህርታዊ ገለፃ ወይም በውይይት ማገዝ ይቻላል፡፡.*

ባለፈው ክፍለ ጊዜ እንደተብራራው ትራኮማ የአይን ችግር የሚያመጣ በሽታ ነው ። ብዙውን ጊዜ በትናንሽ ልጆች ላይ እንደ ቁስለት (infection) እንደ ማቃጥል እና ፈሳሽ ይኖረዋል። ይሁን እንጂ በተደጋጋሚ ከተያዙ በኋላ የዓይን ጠባሳ ሊያስከትልና የማየት ችግር ብሎም ዓይነ-ስውርነት ሊያስከትል ይችላል።

**የ“ማመንን” ስልት:** ትራኮማ በሽታ በግለሰቦችም ሆነ በማህበረሰብ ላይ ከፈፍተኛ ጫና አለው ። ምክንያቱም ልጆች ወደ ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ እና አዋቂዎች ስራ ሰርተው ቤተሰቦቻቸውን መንከባከብ እንዳይችሉ ስለሚያደርግ ነው። በተጨማሪም በአይነ-ስውርነት ምክንትያት ምርታማነትን በመቀነስ በሃገር ኢኮኖሚም ላይ ከፈተኛ ተፅኖ ያስከትላል። በነዚህ ምክንያቶች የዓለም ጤና ድርጅት (WHO) እና የኢትዮጵያ መንግስት የትራኮማ በሽታን ቅድሚያ መጥፋት ካለባቸው በሽታዎች ውስጥ መድበውታል። ትራኮማን ለመከላከል እና ለማጥፋት፣ የዓለም የጤና ድርጅት (WHO) የ“ማመንን” ስልት መጠቀምን ይመክራል፡፡

| ትራኮማን ለመከላከል የ“ማመንን” ስልት | | |
|---|---|---|
| በቀዶ ሕክምና ማከም |  | ወደ ከፍትኛ ደረጃ የደረሰ ወይም አየነ-ስውርነት ሊያደርስ ወደ ሚችልበት ደረጃ ሲደርስ በቀዶ ህክምና ማከም። |
| የፀረ-ተህዋሲያን መድሃኒት (Antibiotics) |  | አብዛኛውን ጊዜ ማህበረሰብ አቀፍ መድሐኒት እደላ ዘመቻዎች በማድረግ አፍለኛ ትራኮማን ፀረ-ተህዋሲያን መድሃኒት (Azithromycine) በመጠቀም ማጥፋት። |
| የፊት ንጽህና |  | በበሽታው ላለመያዝ እንዲሁም ከህክመና በኋላ እንደገና ላለመያዝ፣ እጅ እና ፊትን በሳሙና እና በውሃ እንዲታጠቡ ማበረታታት። |
| የአካባቢ ንጽህናን ማሻሻያ |  | የበሽታውን ስርጭት ለመቀነስ፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦት እና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ፣ በተጨማሪም የዝንቦችን የመራቢያ ቦታ ለመቀነስ የእንስሳትን ቆሻሻ እና የሰውን ዓይነ-ምድር (ሰገራ) በተገቢው መንገድ ማስወገድ። |

የመጀመሪያዎቹ ሁለት የ"ማመንን" ስልቶች ማለትም ቀዶ ሕክምና እና የፀረ-ተህዋሲያን መድሃኒቶች እደላ አፍለኛ ትራኮማን ማከም ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው። ሌሎች ሁለቱ የ"ማመንን" ስልቶች ማለትም የፊት ንጽህናን መጠበቅ እና አካባቢ ጽዳትን ንጽህናን ማሻሻል በበሽታ እንዳይያዙ በመከላከል ላይ ያተኮሩ ናቸው። ትራኮማን በሽታን ለማጥፋት ሕክምናም ሆነ የመከላከያ ዘዴዎችን መጠቀም በጣም አስፈላጊ ነው።

*<u>መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል:</u> በአሁኑ ጊዜ አብዛኛዎቹ የትራኮማ ማጥፋት መርሃግብሮች በመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍሎች ማለትም በቀዶ ሕክምናና በፀረ-ተህዋስያን መድሐኒት እደላ ላይ ብቻ ያተኮረ ነው። እንደ የባህሪ ለውጥ እና የውሃ፣ የአካባቢ ጽዳትና የግል ንፅህና (WASH) በመሳሰሉት የመከላከያ ክፍሎች ላይ ለምን አያተኩሩም?*

*መልስ:* ሰዎች ቀዶ ሕክምና ከተደረገላቸው እና መድሀኒት ከወሰዱ በኃላ በቶሎው ውጤት ስለሚያገኙበት ነው፤ ይህ ደግሞ ለጋሽ ድርጅቶች እና መንግስት ያመጡትን ለውጥ እንዲያሳዩ ይረዳቸዋል። ይሁን እንጂ፣ የውሃ አቅርቦትን ማሻሻል፣ የአካባቢው ጽዳትን መጠበቅ እና የግል ንጽህና ላይ ለውት ማምጠት ሁልጊዜ ሃብት፣ ገንዘብ እና የባህሪ ለውጥ (ፊትን እና የእጅ ንፅህናን መጠበቅ የመሳሰሉትን) ማየት ረጅም ጊዜ ሊወስድ ይችላል እንዲሁም ብዙውን ጊዜ ለመከታተል አስቸጋሪ ነው። ይህ የጤና ትምህርት ፕሮግራም የፊት ንጽህና አጠባበቅ እና የአካባቢ ጽዳት መጠበቅ ስልቶች ላይ ያተኩራል።

## 2.3 የባህሪ ለውጥ

*20 ደቂቃዎች*




*መረጃውን ከተሳታፊዎች ጋር መገምገም፡፡*

መድሃኒት ትራኮማን ለማከም እና ሰዎችን ለህመም የሚያጋልጡ ባክቴሪያዎችን ለመግደል ያስፈልጋል። ጤናማ ለመሆን ወሳኝ እርምጃ በመሆኑ በማህበረሰብ አቀፍ መድሐኒት እደላ ወቅት ተማሪዎች መድሐኒት እንዲወስዱ ማበረታታት ይኖርብናል፡፡

*<u>መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል</u> :* ብዙ ሰዎች መድሃኒቱን ከወሰዱ በኋላ ይሻላቸዋል፡፡ ሆኖም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እንደገና ሊታመሙ ይችላሉ፡፡ ለምን?

*መልስ:* ጸረ-ተህዋስ መድኃኒቶች በወቅቱ በሰውነታቸው ውስጥ ያሉ ተህዋሲያን(ባክቴሪያዎችን) ይገድላሉ። ይሁን እንጂ ሰዎች ከዚህ በፊት ለበሽታው ተጋላጭ እንዲሆኑ ያደረጋቸውን ጤናማ ያልሆኑ ልማዶች ማከናወናቸውን ስለሚቀጥሉ እንደገና በበሽታው ይያዛሉ። በዚህም ምክንያት ይህ የጤና ፕሮግራም የበሽታውን የስረጭት ዑደት ለማቋረጥ በፊት ንጽህና እና በአካባቢ ጽዳት ላይ ያተኩራል።

**ትራኮማ በሽታን የመከላከያ ባሕሪዎች:** የትምህርት ቤቱ ፕሮግራም ትራኮማን መከላከል የሚያስችሉ ጤናማ ባህሪያትን: እንዲሁም ሌሎች ከንፅህና ጉደለት ጋር የተያያዙ በሽታዎችን ሊከላከሉ የሚችሉ ጤናማ ባህሪያትን ያስተምራል። እነዚህ ጤናማ ባህሪያት በአምስት ቁልፍ መልዕክቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። መልዕክቶቹም የግል ንጽሕና መጠበቅን እና አካባቢን ንጹህ ከማድረግ ጋር የተያያዙ ናቸው።

| ቁልፍ መልክቶች | | የግል ባህሪያት |
|---|---|---|
| **ንጹህ እጆች** |  | ወሳኝ በሆኑ ጊዜያቶች እጅን በውሃ እና በሳሙና መታጠብ። |
| **ንጹህ ፊት** |  | ፊትን በውሃና በሳሙና መታጠብ፤ ፊታችንን ለማዳረቅ የምንጠቀምበትን ፎጣ ከሌላ ሰው ጋር በጋራ አለመጠቀም። |
| **ንጹህ አካባቢ** |  | መጸዳጃ ቤት መጠቀም፤ ሜዳ ላይም ሆነ በውኃ መገኛዎች አጠገብ አለመፀዳዳት። |
| **ንጹህ ሰፍራ** |  | ሽንት ቤቱን፣ ክፍሉን እና ግቢውን ማጽዳት። |
| **ጤናማ ጓደኞች እና ቤተሰብ** |  | ጤናማ መልዕክቶችን ለሌሎች መንገር! |

*<u>መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል:</u> በእንተ አስተያየት የትኞቹ ቁልፍ መልእክቶች በአካባቢያችሁ ላሉት ልጆች በጣም ጠቃሚ ናቸው?*

**ንጹህ እጆች:-** እጅን በሳሙናና በውሃ መታጠብ በሽታን ለመከላከል ከሚያስችሉ ዋና ዋና ባህሪያት አንዱ ነው። ትራኮማ ብቻን ሳይሆን ብዙ በሽታዎችን ለመከላከል ይረዳል ። በተጨማሪም በሽታን ለመከላከል በጣም ርካሽ ከሆኑት (ብዙ ዋጋ ከማይጠይቁ) መንገዶች አንዱ ነው ። ትክክለኛ የእጅ አስተጣጠብ ሂደቶች **አባሪ አንድ (Appendex 1)** ላይ ይገኛሉ። መምህራን ለተማሪዎቻቸው ትክክለኛ የእጅ አስተጣጠብ ሂደቶች በተግባር እንዲያሳዩአቸው ይመከራል።

- **ከትራኮማ ጋር ያለው ግንኙነት:-** አንድ የታመመ ሰው ዓይኖቹን ከነካ በኋላ የጤነኛውን ሰው እጅ ይነካል። ከዚያም በቆሸሹ እጆቹ ዓይኖቹን ከነካ ተህዋሲያኑን (ባክቴሪያዎቹን) በማስተላለፍ ሊታመም ይችላል።
- ***ከሌሎች በሽታዎች ጋር ያለው ግንኙነት:-*** ባክቴሪያዎችና ጥገኛ ተውሳኮች በሰገራ አማካኝነት በእጅ አማካኝነት ወደ አፍ በመግባት ሊዛመቱ ይችላሉ። ይህ የሚሆነው አንድ ሰው ከተፀዳዳ በኋላ እጆቹን ሳይታጠብ ምግብ ሲመገብ ነው። ሌላው ቀርቶ 1 ግራም ሰገራ እንኳን በሽታውን ሊያስተላለፍ ስለሚችል ሰዎች እጃቸውን መታጠባቸው በጣም አስፈላጊ ነው!

- ***ወሳኝ የእጅ መታጠብ በጣም ጊዚያቶች :-***

  1) *ምግብ ከመመገብ ወይም ከመንካት በፊት*
  2) *ከመፀዳጃ ቤት ሲመለሱ*

*3) እንስሳትን ከነኩ ወይም ከተጫወቱ በኋላ*

***<u>ለአስተማሪዎቹ የሚሆን ማስታወሻ</u>-*** *ለተማሪዎቻችሁ እንዲህ ብላችሁ ንገሯቸው፣ "እያወቃችሁ ሰገራ ትበላላችሁ? እጃችሁን ሳትታጠቡ ምግብ ከበላችሁ ሰገራ እየበላችሁ ሊሆን ይችላል፤ ባይናችን ማየት የማንችለው አንድ ግራም ሰገራ እንኳን ቢሆን በሽታን ሊያስተላልፍ ይችላል።*

**ንጹህ ፊት፡** ልጆች ትራኮማ እንዳዛቸው ፊታቸውን በሳሙናና በውሃ መታጠብ ይኖርባቸዋል። ፊታቸውን ሲያዳርቁ ከሌሎች ልጆች ጋር በጋራ ሳይጠቀሙ በንጹሕ ፎጣ ማዳረቅ ይኖርባቸዋል ።

- ***ከትራኮማ ጋር ያለው ግንኙነት፡-*** *የቆሸሸ ፊት ዝንቦችን ይስባል፤ ዝንቦች ደግሞ ከታመመ ሕፃን ወደ ጤነኛ ህፃን ትራኮማ ሊያስተላልፉ ይችላሉ። በተጨማሪም ባክቴሪያዎቹ ሰዎች በጋራ በሚጠቅሙባቸው ማዳረቂያ ፎጣዎች ሊተላለፉ ይችላሉ።*
- ***ወሳኝ ጊዜ፡-*** *ፊትን መታጠብ የልጆች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ክፍል መሆን አለበት። በዚህ የጤና ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ 1) ልጆች ከእንቅልፋቸው ሲነቁ ፊታቸውን እንዲያጥቡ እና 2) ከመተኛታቸው በፊት እንዲታጠቡ እናበረታታለን። በተጨማሪም በሚጫወቱበት ጊዜ ከቆሸሹ ፊታቸውን መታጠብ ሊያስፈልጋቸው ይችላል ።*

**ንፁህ አካባቢ፡ ለተማሪዎች በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ሀቆች መካከል አንዱ ሰገራ በሽታን እንደሚያመጣ እና ሊያስተላልፍ እንደሚችል ማስተማር ነው፡፡** አንድ ግራም የሚመዝን ሰገራ እንኳን አደገኛ እና 10 ሚሊዮን ቫይረሶችን ፣1 ሚሊዮን ባክቴሪያዎችንና ከአንድ መቶ በላይ ጥገኛ ተውሳኮችን ሊይዝ ይችላል። እነዚህ ተህዋሲያን ወደ ውሃ መገኛዎቻችን፣ ወደ ልጆቻችን ወይም ወደ ራሳችን እንዲሰራጩ አንፈልግም። በዚህም ምክንያት ተማሪዎች በመጸዳጃ ቤቶች መጠቀማቸው በጣም አስፈላጊ ነው።

| አንድ ግራም ሰገራ ሊይዝ የሚችለው፡- |
|---|
| 10,000,000 ቫይረስ |
| 1,000,000 ባክቴሪያ |
| 100 የጥገኛ ተውሳክ እንቁላሎች |

- ***ከትራኮማ ጋር ያለው ግንኙነት፡-*** *ሰገራ ለዝንቦች መስፋፊያ መቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤ ዝንቦች ደሞ ትራኮማን ማሰራጨት ይችላሉ።*
- ***ከሌሎች በሽታዎች ጋር ያለው ግንኙነት፡-*** *የአንጀት ውስጥ ጥገኛ ትላትሎች እና ብልሃርዚያ በሽታዎች ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት (ሽንት ቤት ካለመጠቀም) ጋር የተያያዙ ናቸው። ዝንቦች ሰገራ ላይ አርፈው ከቆዩ በኋላ በምግባችን ላይ ሲያርፉ ጥገኛ ተህዋሲያንን ሊያሰራጩ ይችላሉ፡፡ ሰዎች በሚጠቀሙበት ውሃ አጠገብ የሚፀዳዱ ከሆነ፣ ለህመም ልንጋለጥ እንችላለን ፡፡*

**ንፁህ ስፍራ፡** ሰዎች አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ስፍራዎች (ከውስጥም ሆነ ከውጭ) ከሰገራ እና ከቆሻሻ ንጹህ መሆን አለባቸው፡ ፡ የቆሸሸ አካባቢ ዝንቦችን በመሳብ በሽታን ያሰራጫል ፡፡

***ከትራኮማ ጋር ያለው ግንኙነት፡-*** *ዝንቦች በቆሸሹ አካባቢዎች ላይ በመራባት ከሰው ወደ ሰው ትራኮማን ያሰራጫሉ ፡፡*

**ጤናማ ቤተሰቦች እና ጓደኞች ፡** የጤና ፕሮግራሙ ስኬታማ እንዲሆን ተማሪዎቹ ጤናማ መልዕክቶችን ለጓደኞቻቸው እና ለቤተሰቦቻቸው መንገር ይኖርባቸዋል፡፡ ተማሪዎቹን የጤና መልእክተኞች በማድረግ ለሌሎች አርአያ መሆን ስለሚጠበቅባቸው

በራሳቸው ባህሪ ላይ የበለጠ ባለቤትነት ይሰማቸዋል፡፡ በተጨማሪም ቤተሰቦቻቸው በቤት ውስጥ ጤናን ለማሻሻል ለውጦችን ማምጣት መጀመር እንዲችሉ ያደርጋቸዋል።

*<u>መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል</u>* : መምህራን በሽታን በመከላከል ረገድ ከፍተኛ ሚና አላቸው። ተማሪዎቹ ልማዳቸውንና ጠባያቸውን ወደ ጤናማ ባህሪያት ለመለወጥ ማስተማር ብቻ ሳይሆን አስተማሪዎቹ እነዚህ ባሕርያት ለተማሪዎቻቸው ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ በተግባር ማሳየት የሚችሉት እንዴት ነው?

## 2.4 በርካታ ነገሮችን በአንዴ የማድረግ/የአስተሳሰብ ክህሎቶች

*20 ደቂቃዎች*

*መረጃውን ከተሳታፊዎች ጋር መገምገም ፡፡ ይህንን ክፍል ትምህርታዊ ገለፃ ወይም በውይይት መደገፍ ይቻላል ፡፡*

ሁሉም ሰዎች የተለያዩ ችሎታዎች ፣ ጥንካሬዎች እና ድክመቶች አሏቸው ፣ ሁላችንም በትንሹም ቢሆን በተለያዩ መንገዶች እንማራቸዋለን። ሆኖም ፣ ቀደም ባሉት ጊዜያት ባህላዊ የሆነ የትምህርት አሰጣጥ ጠበብ ባለ የማሰብ ችሎታ እይታ ላይ ብቻ ያተኮረ ነበር፡፡ በዚህም ብዙ ተማሪዎች ወደኋላ ቀርተዋል ወይም በችሎታቸው ላይ እምነት አጥተዋል ፡፡ በዚህ ምክንያት፣ ብዛሀነት ያለው የማሰብ ችሎታ  በፅንሰ-ሀሳብ ቀርቧል ፡፡ ምንም እንኳን አንዳንድ ተማሪዎች በትምህረታዊ ገለፃ መልክ በሚሰጡ ትምህርቶች የላቀ ውጤት ሊያገኙ ቢችሉም ፣ ሌሎች ሀሳቦችን በአይን በማየት ወይም በእጃቸው አንድ ነገር በማድረግ ሊያንፀባርቁ የቻላሉ ፡፡ ስለሆነም መምህራኖች ሁሉንም ተማሪዎቻቸውን ተደራሽ ለማድረግ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መጠቀማቸው አስፈላጊ ነው ፡፡

ተማሪዎች እንዴት እንደሚማሩ እና እንዴት በማሰብ ችሎታ ብልጫ እንደሚወስዱ በተሻለ መልኩ ለመረዳት ስምንት ዓይነት ችሎታዎች ተለይተው በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ውስጥ ተዘርዝረዋል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በእያንዳንዱ ውስጥ የተለያየ ደረጃ ያለው ችሎታ እንደላቸው ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ ባህላዊ ተማሪዎችም እንኳ ከሌሎች አቀራረቦች (እንደ ሥዕላዊ እና ጨዋታ-ተኮር ያሉ) ተጠቃሚ ይሆናሉ። ተማሪዎቻቸው የላቀ ውጤት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ መምህራን በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ቢያንስ 2-3 የተለያዩ ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ እንመክራለን ፡፡

| ችሎታ | ጥንካሬዎች | ለመማርያ ክፍሉ ውስጥ የሚሆኑ ዘዴዎች |
|---|---|---|
| **በምስል ላይ ጎበዝ (vision)** | ስዕሎችን ፣ ግራፎችን እና ካርታዎችን በመተርጎም፤ ጥሩ ሥዕል በመሳል እና ቀለም በመቀባት ይደሰታል፤ ንድፍ (Pattern) በቀላሉ ይገነዘባል። | ስዕል፤ሀሳቦችን ለማሳየት ስዕሎችን እና ሰንጠረዦችን/ካርታዎችን በመጠቀም። |
| **ቃል ላይ ጎበዝ (ንግ ግር)** | በጽሑፍ እና የንግግር የሚገኙ መረጃዎችን ማስታወስ ላይ ጥሩ ነው፤ ማንበብ እና መፃፍ ያስደስተዋል፤ ሀሳቦችን በሚገባ ያብራራል። | ንባብ፤መጻፍ፤ ውይይቶች፤ ተረት ተረት። |
| **ቁጥር ላይ ጎበዝ (ሂሳብ)** | ችግሮችን በመፍታት ረገድ ጥሩ ነው፤ ረቂቅ ሀሳቦችን በማሰብ ይደሰታል፤ በደንብ ያሰላል | ሙከራዎችን ማድረግ ፤ ችግሮችን በመፍታት፤ ሂሳብ እና አመክንዮ (logic) የሚጠቀሙ |

| | | |
|---|---|---|
| | እንዲሁም ጭብጦችን ያሰላስላል ። | ጨዋታዎችን መጫወት። |
| **የሰውነት እንቅስቃሴ ላይ ጎበዝ (ቆንጆ)** | ዳንስ እና ስፖርት ላይ ጥሩ ነው፤ በእጆቹ ነገሮችን በመፍጠር ይደሰታል፤ ማድረግ/በመተግበር ይማራል። | በንቃት ጨዋታዎች በመጫዎት፤ ፅንሰ-ሀሳቦችን በተግባር ማሳየት፤ ነገሮችን መገንባት። |
| **ሙዚቃ ላይ ጎበዝ (ሙዚቀኛ)** | በጥሩ ሁኔታ ዘፈኖችን እና ዜማዎችን ማስታወስ ፤ በመዝፈን እና የሙዚቃ መሳሪያዎች በመጫወት ይደሰታል፤ የሙዚቃ ኖታዎችን እና የሙዚቃ ንድፎችን በቀላሉ ያውቃል። | ፅንሰ፡ሀሳቦችን ለማስተማር ዘፈኖችን እና ዳንሶችን/ጭፈራዎችን መጠቀም፤ ግጥም ፤ በጭብጨባ ሁነቶችን ማስታወስ ። |
| **ከሰዎች ጋር በመግባባት ጎበዝ (ግለሰባዊ)** | ጥሩ ተግባቦት፤ሁኔታዎችን ከተለያዩ እይታዎች መመልከት ፤ ግጭቶችን መፍታት መቻል። | የቡድን ሥራ፤ የአቻ ለአቻ መማማር፤ ጨዋታዎች። |
| **የራስን ጥንካሬ ማወቅ ላይ ጎበዝ (ግለሰባዊ)** | የራሱን ጥንካሬና ተነሳሽነት በመተንተን ጥሩ የሆነ፤ ሀሳቦችን እና የራሱን ስሜት በመተንተን ይደሰታል፤ ስለራሱ እጅግ በጣም ጥሩ ግንዛቤ መኖር። | የህትመት ጽሑፍ፤ ግብ የማስቀመጥ ተግባራት፤ ማንጸብራቅ። |
| **ተፈጥሮ ላይ ጎበዝ (ተፈጥሮአዊ)** | እፅዋትን እና እንስሳትን በመለየት እና በመመደብ ጥሩ መሆን፤ በተፈጥሮ ውስጥ በመሆኑ ይደሰታል፤ ለሳይንስ ፍላጎት ይኖረዋል። | በተፈጥሮ መንሸራሸር፤ ርዕሶችን ከተፈጥሮው ዓለም ጋር ማገናኘት፤ የትምህርት ቤት ቅጥር ግቢን ማጽዳት ወይም የአትክልት መትከል መጀመር። |

በማጠቃለያ ሁሉም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን በመደመር ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ብዙዎቹ ተማሪዎች ትምህርቱን ለመረዳት ይችላሉ፤ እንዲሁም የተለያዩ ተግባራት ለሁሉም የበለጠ ትኩረት የሚስብ ያደርግላቸዋል። እንደ **ማስታወሻ**፤ መምህራን ብዙ ነገሮችን ባንዴ የማድረግ ችሎታ እና ተግባራት ማግኘት አያስፈልጋቸውም። ሁሉም ሰዎች ብዙ አይነት ችሎታዎች አሏቸው፡፡ እናም ከትንሽም ቢሆን ጥቅም ያገኛሉ ፣ ስለሆነም የመማሪያ ይዘቱን ሳይቀንሱ ድብልቅ ተግባራት ላይ ያተኮሩ ያስፈልጋል።

*መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል:*

1. *በመከፈቻ ተግባራት ላይ በመመርኮዝ በዚህ ቡድን ውስጥ የትኞቹ ችሎታዎች የተለመዱ ናቸው?*
2. *በትምህርቱ ውስጥ ከ2-3 የተለያዩ የተግባራት ዓይነቶችን እንዲያካትቱ እንመክራለን፡፡ ሁሉንም አይነት ችሎታዎች በትምህርቱ ሂደቱ ውስጥ መጠቀማችንን ለማረጋገጥ 8 ዓይነት ተግባራትን ማካተት ለምን አልተመከረም?*

## 2.5 ተግባር፡ መዝሙሮች

*40 ደቂቃዎች*

*ከተሳታፊዎች ጋር በመሆን የሚከተሉትን መመሪያዎች በመመልከት በቡድን ሆነው እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ አካሄዳቸውን ለመከታተል እና ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት በክፍሉ ውስጥ መንቀሳቀስ እና በዚህ ክፍል ውስጥ ተሳታፊዎች በንቃት እንዲሰሩ መድረግ፡፡*

ክፍል ሁለትንን ለማጠናቀቅ፣ ተሳታፊዎች እጅና ፊታቸውን እንዴት እና መቼ በሚገባ መታጠብ እንዳለባቸው ለማስተማር የሚጠቀሙበትን መዝሙር ለማዘጋጀት ተሳታፊዎቹ በጋራ ይሰራሉ። ይህ መዝሙር ተማሪዎችን በመዝሙር ችሎታ ለማሳተፍ እንደ አንድ መንገድ ሊያገለግል ይችላል። ተማሪዎች አስፈላጊ መረጃዎችን እንዲያስታውሱ እና ትምህርቱ ለእነሱ የበለጠ አዝናኝ እንዲሆን ለማድረግ መዝሙሮች እና ግጥሞች ጥሩ መሣሪያ ናቸው፡፡

*ለመዝሙር መመሪያዎች:*

1. ተሳታፊዎች ከ4-8 ሰዎች በመሆን ቡድን እንዲሰሩ ንገራቸው፡፡
2. እጃቸውንና ፊታቸውን በሳሙናና በውኃ ለመታጠብ ስለሚያስችሏቸው ወሳኝ ጊዜያት የሚገልጽ መዝሙር እንደሚሰሩ ንገሯቸው። መዝሙሩ ሌሎች የትራኮማ በሽታ የመከላከያ ባህሪያትንም ሊያካትት ይችላል፤ ነገር ግን በተማሪው የትምህርት እቅድ ውስጥ ከሚከናወነው ተግባር ጋር በተያያዘ ቁልፍ ጊዜዎችን ማካተት ይኖርበታል።
3. መዝሙሩ በአካባቢያቸው ቋንቋ መሆን አለበት፤ እንዲሁም በሌላ ታዋቂ ዘፈን ላይ የተመሠረተ በአዳዲስ ቃላት መተካት ሊሆን ይችላል።
4. ቡድኖቹ ሲሰሩ ስራቸውን ለመከታተል እና ለጥያቄዎቻቸው መልስ ለመስጠት በክፍል ውስጥ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል።
5. ከ15-20 ደቂቃ በኋላ የተወሰኑትን ቡድኖች መዝሙሮቻቸውን ለሁሉም እንዲያቀርቡ ማድረግ።
6. ጊዜ ካለ፣ ተሳታፊዎች የወደዱትን መዝሙር ላይ ድምጽ እንዲሰጡ በማድረግ የመረጡትን መዝሙር ሁሉንም በአንድ ላይ እንዲማሩት ማድረግ፡፡
7. *ጥያቄ*

- መዝሙር በሰውነት እንቅስቃሴ ኀበዝ ለሆኑ ተማሪዎችም እንዲሆን እንዴት ማመቻቸት ይችላሉ?
- በክፍላችሁ ውስጥ የእይታ ተማሪዎች አሉ፤ እነርሱን ስለ ተራኮማ በሽታ መከላከያ ባህሪያትን እንዴት ማስተማር ይችላላል?

**መዝሙር:**

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

*** ማስታወሻ:** አስተማሪዎች መዝሙሩን ከ1-5 ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎቻቸውን ለማስተማር ይጠቀሙበታል ፡፡

# ክፍል 3፡ ታሪኮችን (ተረቶችን) በመንገር ግንኙነቶች መገንባት

## 3.1 ቁልፍ የሆኑ አነቃቂ መልዕክቶች *10 ደቂቃዎች*

*አመቻቹ ተሳታፊዎቹን አምስቱን ቁልፍ መልዕክቶች በየመሀሉ በማጨብጨብ የሚናገሩበት መልመጃ እንዲሰሩ ይመራቸዋል ፡፡*

ባለፉት ሁለት ክፍሎች፣ የትራኮማ በሽታን መተላለፊያ መንገዶች እና መከላከል ዘዴዎችን እንዲሁም በተለያዩ የመማር ማስተማር ስልቶች ላይ ተወያይተናል ፡፡ የተወሰኑ መረጃዎችን ለመገምገም እና ቡድኑን ዘና እንዲል ለማድረግ በቁልፍ መልዕክቶች ላይ አጭር ልምምድ እናደርጋለን ፡፡

*መመሪያዎች ለቀልዶቹ፡*

1. **አመቻቹ "አሁን በ5 ቁልፍ መልዕክቶች እና በየመሐሉ በማጨብጨብ ክፍል 3ን እንከፍታለን" ይላል።**
2. **አመቻቹ ከቁልፍ መልዕክቶች አንዱን (ንጹህ እጆች) ይልና ሁሉም አንድ ጊዜ አብረው ያጨበጭባሉ።**
3. **አንድ ሌላ ተሳታፊ ቁልፍ መልዕክት እንዲናገር መጠቆምና ሁሉም ሰው እንደገና አንድ ላይ ያጨበጭባል።**
4. **ከዚያም ያ ሰው ሌላ ቁልፍ መልዕክት ለሚል ሌላ ተሳታፊ ይጠቁም ወዘተ...።**
5. **ደግመው ደጋግመው ግን በፍጥነት ማለት።**

*ጥያቄ:*

- በመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍሎች ላይ ማንኛውም አይነት ጥያቄዎች አሏችሁ?

## 3.2 የልጅነት እድሜ *15 ደቂቃ*

*መረጃውን ከተሳታፊዎች ጋር መገምገም፡፡ ይህንን ክፍል ትምህረታዊ ገለፃ ወይም በውይይት መደገፍ ይቻላል።.*

**ልጅነት ዕድሜ ላይ ማተኮር፡** በትናንሽ ልጆች ላይ በተለየ ሁኔታ ትኩረት የሚያደርግ የትራኮማ የጤና ትምህርት ፕሮግራም ለመተግበር ብዙ ምክንያቶች አሉ። ለምሳሌ ፡

- ትናንሽ ልጆች በበሽታው የመያዝ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው ፡፡ በልጅነት ጊዜ በተደጋግሚ በበሽታው መጠቃት በአዋቂነት እድሜ ላይ ወደ ዓይነ-ስውርነት ያደርሳል ፡፡
- በልጅነት ዕድሜ ውስጥ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የሚቀረጹት በልጆች እድሜ ላይ የተወሰኑ ባህሪያትን እና ልምዶችን ለመፍጠር ነው፡፡ ቀደም ብለው በልጅነት ዕድሜ የተለመዱ ባህሪያት እና ልምዶች ለዓመታት የሚቀጥሉ እና ለወደፊቱም በሽታን የመከላከል ዕድላቸው ሰፊ ነው ፡፡

- ቀደም ብለን ያጎለበትናቸው ባሕርያትና ልማዶች ለዓመታት አብረውን የመቀጠል እድላቸው ሰፊ ሲሆን እንደገና በበሺታው መያዝንም ይከላከላል።
- ትናንሽ ልጆች በቀላሉ ሊቀረጹ የሚችሉና ከሁኔታዎች ጋር ራሳቸውን ማስማማት የሚችሉ ለለውጥ የሚስማሙ ናቸው። ከወጣቶች እና ጎልማሶች በበለጠ ፍጥነት እና በቀላሉ አዳዲስ ልምዶችን መማር እና መቀበል ይችላሉ።
- ልጆች የተማሩትን መረጃ በማስተላለፍ በሌሎች ላይ ተጽዕኖ የማድረግ ችሎታ አላቸው፤ ስለሆነም በቤተሰቦቻቸው ላይ የባህሪ ለውጥ እንዲመጣ ያበረታታሉ እንዑም በቤተሰብ ውስጥ የንፅህና አጠባበቅ ልምዶችን ያሻሽላሉ ፡፡

**የህፃናት እድገት:** ሕጻንነት (0-8 ዓመት) በሰው ልጅ እድገት ውስጥ ወሳኝ ወቅት ተደርጎ ይቆጠራል፣ አካላዊ፣ ማኅበራዊ ስሜታዊና የማሰብ ችሎታ ማዳበርን ጨምሮ በሁሉም የሕይወት ዘርፎች አስገራሚ ለውጦች ይከሰታሉ። ይህ ወቅት አንድ ሰው ማን እንደሚሆን የሚቀርጽበት ወሳኝ የሆነ ጊዜ ነው ። የልጅነት ትምህርት፥ በማሰብ ችሎታ፣ ባሕርይና የወደፊት የሥራ ዕድል ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ጥናቶች አመላክተዋል። በዚህም ምክንያት የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና ሌሎች ፖሊሲ አውጪዎች የልጅነት ትምህርት ለጤና፣ ለኢኮኖሚና ለሀገር ዕድገት ትልቅ ኢንቨስትመንት እንዲሆን ማበረታታት ጀምረዋል።

የሚከተሉት 5 ነገሮች በልጅነት ጊዜ ይዳብራሉ፡

| በልጅነት ጊዜ እድገት የሚታይባቸው ጉዳዮች/ነገሮች | |
|---|---|
| **በሽታን የመቋቋም አቅም** | በሽታ ተከላካይ ሕዋሳት የሚፈጠሩት ገና በለጋ ዕድሜ ሲሆን የአንድን ሰው የእድሜ ዘመን ጤንነት ይወስናሉ። |
| **ባህሪያት እና ልማዶች** | ትንንሽ ልጆች በቀሪው የሕይወት ዘመናቸው አብረዋቸው የሚኖሩ ልማዶችንና ባህሪያትን ይማራሉ ። |
| **እርስ-በርስ ግንኙነት እና የሐሳብ ልውውጥ** | ልጆች ከሌሎች ሰዎች እና ከአካባቢያቸው ጋር ለመግባባት እና የሐሳብ ልውውጥ ለማድረግ ክህሎቶችን ይገነባሉ ፣ ይህም በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በሚኖራቸው መልካም ግንኙነቶች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል ፡፡ |
| **በጨዋታ ውስጥ መማር** | ልጆች በጨዋታዎች፣ በመዝሙሮች እና በድራማዎች በጣም ውጤታማ በሆነ መንገድ ይማራሉ።<br>– በጨዋታ መሃል መማር እንዴት ከሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር እንዳለባቸው መረዳት እንዲችሉ ያግዛቸዋል። |
| **ማሰብ እና ቋንቋ** | በእነዚህ የእድገት ዓመታት ውስጥ የቋንቋ እና የአስተሳሰብ እድገት ወሳኝ ነው፡፡ ለዚህም ነው ከልጆች ጋር መነጋገር ፣ ነገሮችን በጥልቀት ማስረዳት ፣ ጥያቄዎችን መጠየቅ እና ታሪኮችን መንገር አስፈላጊ የሆነው፡፡ |

*መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል ፦ ትናንሽ ልጆች (1ኛ ክፍል) ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ የሚማሯቸው አንዳንድ አዳዲስ ባህሪዎች ምንድ ናቸው፧*

*ሊሆኑ የሚችሉ መልሶች:* በክፍል ውስጥ እጅን ማውጣት፣ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ሰልፍ መቆም ፣ መፀዳጃ ቤት መሄድ (ቤታቸው መፀዳጃ ከሌላቸው) ወዘተ ::

## 3.3 መልዕክት ማስተላለፊያ ስልቶች *10 ደቂቃዎች*

*መረጃውን ከተሳታፊዎች ጋር መገምገም :: ይህንን ክፍል ትምህርታዊ ገለፃ ወይም በውይይት መደገፍ ይቻላል ::*

**የባህሪ ለውጥ:** የባህሪ ለውጥ ማምጣት ቀላል ተግባር አይደለም፤ ጤናማ ባህሪ ከመማር በላይ የሆኑ ነገሮችን ያካትታል። ሰዎችም ለመለወጥ ተነሳሽነት እና ልምምድ ይፈልጋሉ :: ስለ በሽታ የመከላከያ ባህሪያት ትናንሽ ልጆችን ሲያስተምሯቸው ሊረዱ የሚችሉት አንዳንድ ስልቶች እዚህ ተጠቅሰዋል፥:

- ✓ **ባህሪውን በማሳየት ሞዴል መሆን** - ህፃናት ሌሎችን በማየት እና ከሌሎች በመኮረጅ ባህሪያትን ይማራሉ :: እጃቸውን እና ፊታቸውን እንዴት እንደሚታጠቡ ማሳየት እና እነሱም እንዲለማመዱ ማድረግ ይቻላል::
- ✓ **ስሜታዊ ግንኙነትን መገንባት**- ከልብ ወለድ ገጸ-ባህሪያት ጋር ማገናኘት እና በድርጊቶቻቸው ላይ መመሰጥ ስለሚችሉ ትናንሽ ህፃናትን ለማስተማር ተረት-ተረት ጥሩ መሣሪያ ነው ::
- ✓ **ተማሪዎች እንደአስተማሪዎች እንዲሆኑ መጠየቅ** - ምላሽ ሰጭ ተረት ተማሪዎች በልብ ወለድ ታሪክ ውስጥ እንዲሳተፉ ይጠይቃል :: ገጸ-ባህሪያቱ ግባቸውን ለማሳካት እንዴት ሊረዷቸው ይችላሉ? ለሌሎች ባህሪያትን ሞዴል እንዲያደርጉ እና አስፈላጊ የጤና መልዕክቶችን በማሰራጨት እንደ አስተማሪ ሆነው እንዲሠሩ መጠየቅ::
- ✓ **ምናባዊነት (በዓይነ ሕሊና የማየት ችሎታን) እና የፈጠራ ችሎታን ማዳበር** - ምናባዊነት (በዓይነ ሕሊና የማየት) ለህፃናት አዕምሮ እና ማህበራዊ እድገት ወሳኝ መሳሪያ ነው። በምናባዊ መንገድ ተማሪዎች አዳዲስ ሃሳቦችን መጫወት እና የሚማሩትን ነገር ሙከራ ማድረግ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች መፍጠር ይችላሉ።
- ✓ **በሁለንተናዊ ችሎታ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ** - ተማሪዎቹን በሥዕል፣ በዘፈን እና በተለያዩ ድርጊች ላይ ማሳተፍ። በተሻለ መልኩ በጉዳዩ ላይ ገብተውበት በውስጣቸው እንዲቀመጥ የሚያደርግ ተጨማሪ መንገድ ይፈጥራል።
- ✓ **ድግግሞሽ መፍጠር** - ልጆች የዕለት ተዕለት ሕይወታቸው አካል ከሆነ ባህሪያቶችን ያስታውሳሉ ። አስተማሪዎች በየቀኑ እጃቸውን ለመታጠብ ወይም የፊት ንጽሕናን ለመቆጣጠር የተወሰነ ጊዜ ሊመድቡ ይችላሉ፤ ይህ ከሆነ ተማሪዎቹ ይህን ጊዜ መጠበቅና ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው ያውቃሉ።

*መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል:* *ትናንሽ ልጆችን (ከ 0 እስከ 8 አመት) ለማስተማር ሌሎች ስልቶችን ያውቃሉ?*

## 3.4 ተረት *10 minutes*

*መረጃውን ከተሳታፊዎች ጋር መገምገም :: ይህንን ክፍል በ ትምህርታዊ ገለፃ ወይም በውይይት መደገፍ ይችላል ::*

ተረት በጣም ጥንታዊ እና ውጤታማ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አንዱ ነው :: አንድ ታሪክ ቁልፍ የሆኑ መልእክቶችን በምሳሌ ለማስረዳትና አስፈላጊ የሆኑ ሐሳቦችን ለተማሪዎች በሚጠቅምና ከትምህርቱ ጋር ይበልጥ ሊያገናኝ የሚችለውን መንገድ ሊያስተምር ይችላል። አድማጮች መረጃው እንደ ወረደ ቀርቦ ከሚሰማቸው ይልቅ ከገጸ ባሕርያቶቹ ጋር ስሜታዊ ወይም የግል ግንኙነት

እንዳላቸው ሊሰማቸው ይችላል። ከዚህም በላይ ታሪኮች በዓይነ-ሕሊና የማየት ችሎታ እንዲኖራቸው በማድረግ የአድማጮችን አዕምሮ የሚያንቀሳቅሱ ናቸው።

**በክፍል ውስጥ:** በክፍል ውስጥ ታሪኮች በሚጠቀሙበት ጊዜ ተማሪዎች ታሪኩን በአእምሯቸው ውስጥ በዓይነ-ሕሊናቸው መሳል፣ ምን ሊፈጠር እንደሚችል መገመት፣ በጥልቀት የማሰብ ችሎታቸውን በመጠቀም በታሪኩ ላይ መጨመር ወይም በውስጡ ያሉትን ችግሮች መፍታት ይችላሉ። እነዚህ ተግባራቶች የተማሪዎቹን የማዳመጥና የመናገር ችሎታ ያሻሽላሉ። በተጨማሪም ተረት መናገር ተማሪዎች በራሳቸው ላይ እምነት እንዲያድርባቸውና ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ ሊያነሳሳቸው ይችላል ።

የሚከተሉት ጠቃሚ ምክሮች ተረት ስሜትን ይበልጥ የሚቀሰቅስ እንዲሆን ያደርጋሉ፡-

- ✓ **ድምፆችን መጠቀም:** ከገጸ-ባህሪያት ጋር መጫዎት እና ለእያንዳንዳቸው የተለያዩ ድምፆችን መጠቀም።
- ✓ **የሰውነት እንቅስቃሴን መጠቀም:** ቁልፍ የሆኑ ነጥቦችን ወይም ድርጊቶችን በምሳሌ ለማስረዳት በአካላዊ እንቅስቃሴ መግለጽ።
- ✓ **በታሪኩ ላይ መጨመር** - ትረካውን ለማበልጸግ መብራሪያዎችን መጨመር።
- ✓ **ተማሪዎች ምላሽ እንዲሰጡ መጠየቅ** - ቀጥሎ ምን እንደሚከሰት ለመገመት ወይም በታሪኩ ውስጥ አዳዲስ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ዓይነ-ሕሊናቸውን እንዲጠቀሙ ማድረግ። በታሪኩ ላይ በንቃት ምላሽ እየሰጡ ከሆነ በይበልጥ ይመሰጣሉ።
- ✓ **ታሪኩን በአካባቢው ካለው ሁኔታ ጋር ማስተካከል** - ተማሪዎች በታሪኩ ውስጥ ከሚከናወነው ነገር ጋር የበለጠ ግንኙነት እንዳላቸው እንዲሰማቸው የአካባቢውን ስፍራ ስሞችና ሁኔታዎች መጠቀም።
- ✓ **ታሪኩን በሚናገሩበት ጊዜ ዘና ማለት** - አንተን የሚያስደስትህ ከሆነ ተማሪዎችም ይደሰቱበታል። አዝናኝና አስቂኝ የሆነ የድምፅ ቃና ተጠቀም።

*መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል*: በአካባቢያችሁ ውስጥ ላሉ ልጆች የሚሆን ታዋቂ ተረት ምንድነው፤ ሊያስተምር የሚችለው ማንኛውንም አይነት ጠቃሚ ትምህርት ምንድነው?

## 3.5 የትግበራ መጽሐፍ

*45 ደቂቃዎች*

*የሚከተሉትን መመሪያዎች ከተሳታፊዎች ጋር መመልከት እና በቡድን ሆነው እንዲሰሩ መድረግ ፡፡ ስራቸውን ለመከታተል እና ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት በክፍሉ ውስጥ መንቀሳቀስ ይቻላል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ተሳታፊዎች በንቃት እንዲሰሩ መድረግ ያስፈሊጋል ፡፡*

ከ1-2 ክፍል ላሉ ተማሪዎች፣ መምህራን ስለ ትራኮማ ለማስተማር እና በልጆች ላይ ጤናማ ባህሪያትን ለማነሳሳት **የጤናማ ጓደኞች የታሪክ** መጽሐፍን መጠቀም። ይህ ታሪክ መጽሃፍ አሳታፊ እና እንዲመሰጡ ለማድረግ ገጸ-ባህሪያትን፣ ተግባራትን እና ጥያቄዎችን የያዘ የትግበራ መፅሐፍ ነው። የትግበራ መጽሐፉን ሁሉም እንደሚጠቀሙበት እርግጠኛ ለመሆን፣ በትግበራ መጽሐፉ ለመለማመድ እና በተቻለ አቅም አሳታፊ እንዲሆን ለማድረግ አሁን ትንሽ ጊዜ እንወሰዳለን፡፡ መምህራንም በክፍል ውስጥ ከተማሪዎች ጋር ከመጀመራቸው በፊት መጽሐፉን ለመለማመጃ በቂ ጊዜ እንዳገኙ እርግጠኛ መሆን ፡፡

*የታሪክ መጽሐፍ መመሪያዎች*

1. ተሳታፊዎች ከ4-8 ሰዎች በመሆን ቡድን እንዲሰሩ መንገር፡፡
2. እያንዳንዱ ቡድን **የጤናማ የጓደኞች ታሪክ መጽሐፍ** እና **የአስተማሪውን መጽሐፍ** **ቅጂዎች** መኖራቸውን ማረጋገጥ።
3. **በአስተማሪው መጽሐፍ** (**ክፍል 3**) ውስጥ ከ 1-2 ኛ ክፍል ያሉትን የትምህርት እቅድ በመጀመሪያ እንዲያነቡ መንገር ፡፡
4. ከዚያ አንድ ሰው የ "አስተማሪ" ሚናውን ይረከብና የተማሪዎቹን ገጸ-ባህሪዎች በመተንተን እና የተማሪዎችን መልሶች በማበረታታት የታሪኩን መጽሐፍ ያነባል ፡፡
5. "አስተማሪው" ከጨረሰ በኋላ "ተማሪዎች" የታሪኩ አቀራረብ ላይ ሊሻሻሉ በሚችሉ ክፍሎች ላይ አስተያየት ይሰጣሉ። ከላይ ያሉትን ምክሮች በ 3.4 ውስጥ መመልከት ይችላሉ ፡፡
6. ከዚያ ሌላ ሰው ደግሞ የ "አስተማሪ" ሚና ይረከብና የታሪኩን መጽሐፍ ያነባል ፤ ታሪኩን በተቻለ መጠን አሳታፊ ያደርገዋል።
7. *ጥያቄ*
    - ከታሪኩ መጽሐፍ ግልፅ ያልነበሩ ክፍሎች ነበሩ?
    - መምህራን በታሪኩ መጽሐፍ ላይ ጭውውት/ድራማ እንዴት ሊጨምሩ ይችላሉ? መጽሐፍን ለማስፋት ምን ሌሎች ነገሮችን መጨመር ይችላሉ?

# ክፍል 4፡ ተነሳሽነት ለመፍጠር እና ግብ-ለማስቅመጥ የሚሆኑ ጨዋታዎች

## 4.1 የእጅ አስተጣጠብ በተግባር ማሳየት

*15 ደቂቃዎች*

*ሁለት ፈቃደኞች እንዲመጡ በመጠየቅ ለሁሉም ተሳታፊዎች ትክክለኛውን የእጅ አስተጣጠብ እንዲያሳዩ ማድረግ፡፡*

ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ እጅን በሳሙና እና በውሃ መታጠብ ሰዎች ሊያደርጓቸው ከሚችሏቸው እጅግ በጣም አስፈላጊ የጤና ባህሪዎች አንዱ ነው ፡፡ ትራኮማ ፣ የአንጀት ትላትሎች እና ሌላው ቀርቶ ኮቪድ-19ን (COVID-19) ጨምሮ በርካታ በሽታዎች እንዳይስፋፉ ለመከላከል በጣም አስፈላጊ ነው ፡፡ በዚህ ምክንያት ተማሪዎች እጃቸውን በትክክል እየታጠቡ ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን እንፈልጋለን ፡፡ እጅን ለመታጠብ የሚደረጉ ሂደቶች በአባሪ 1 የተጠቀሱት ናቸው፤ አሁን ሁለት ፈቃደኛ ተሳታፊዎች የእጅ አስተጣጠብን እንዴት ለተማሪዎች ማስተማር እንደሚችሉ ያሳያሉ።

*<u>የሰርቶ ማሳያ መመሪያዎች</u>*

1. ሁለት ፈቃደኛ ተሳታፊውችን ፊት ለፊት እንዲመጡ መጠየቅ ፡፡ አንደኛው እንደ “አስተማሪ” ይሆን እና ሌላኛው ደግሞ እንደ “ተማሪ” ይሆናል፡፡
2. የእጅ መታጠቢያ እቃ የመታጠቢያ ሳህን ፣ ውሃ ፣ ሳሙና እና ንጹህ ፎጣን ጨምሮ ይሰጣቸው ፡፡
3. “አስተማሪው” **በአባሪ 1** ላይ ያሉትን የእጅ አስተጣጠብ ሂደቶችን በመጠቀም “ተማሪዎችን” እጃቸውን በትክክል እንዴት መታጠብ እንዳለባቸው ያስተምራል ፡፡

*ጥያቄ*

- በአካባቢያችሁ ውስጥ ያሉ ትምህርት ቤቶች ለእጅ መታጠቢያ የሚሆን የውሃ አቅርቦት አላቸው?
- ተደራሺነት ከሌላቸው ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸው አንዳንድ መፍትሄዎች ምንድናቸው?

*ሊሆኑ የሚችሉ መልሶች:* የመጠጥ ውሃን ያህል ንጹህ መሆን ስለማይጠበቅበት ፣ ተማሪዎች ለእጅ መታጠቢያ የሚጠቀሙበትን ውሃ በተራ ማምጣት ይችላሉ፡፡ የወላጅ፣ መምህራን ህብረቱ ለሳሙና እና የእጅ መታጠቢያ እቃዎች የሚሆን በጀት መመደብ ፡፡.

**ማስታዎሻ፡** ሁለት ዓይነት የእጅ አስተጣጠብ በማስተማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ተካትተዋል ፡፡ አሁን ያሳየናቸው የእጅ አስተጣጠብ ሂደቶች **በአባሪ 1** እና ከ2-5 ክፍል እንዲሁም በተማሪ ክበባት የትምህርት እቅዶች ውስጥ ተካተዋል ፡፡ የትንንሽ ልጆች (ከ1-2ኛ

ክፍል) የታሪክ መጽሐፍ ላይ ቀለል ያለ ፊትን የመታጠቢያ ዘዴ ተካቷል ፡፡ ይህ አማራጭ ለትንንሽ ልጆች በቀን ሁለት ጊዜ የሚያደርጉትን የፊት ንጽህና የዕለት ተዕለት ተግባራቸው አካል ለማድረግ የቀረበ ነው ፡፡ ይህ አማራጭ **በአባሪ 2** ላይም ቀርቧል ፡፡

## 4.2 በክፍል ውስጥ ጨዋታዎችን መጠቀም *15 ደቂቃዎች*

*መረጃውን ከተሳታፊዎች ጋር መገምገም ፡፡ ይህንን ክፍል ትምህርታዊ ገለፃ ወይም በውይይት መደገፍ ይቻላል።*

የትምህርት ቤቱ መርሃ ግብር ትምህርትን ለማሻሻል እና ከንፅህና ጋር ተያያዥነት ያለው የባህሪ ለውጥን ለማምጣት ሁለት ጨዋታዎችን ያካትታል። ከ2-5 ኛ ክፍል ተማሪዎች **የንፁህ ካፕቴን ቦርድ ጨዋታ** የተካተተ ሲሆን በሚቀጥለው ክፍል ልምምድ ይደረግበታል ፡፡ ለጤና እና **ዋሽ ክበባት የሥነ-ንጽህና ጀግኖች ፈታኝ ጨዋታ** የተካተተ ሲሆን በ 4.4 ውስጥ በበለጠ ዝርዝር ይቀርባል ፡፡

**ለመማር የሚሆኑ ጨዋታዎች:** አስተማሪዎች በክፍል ውስጥ ጨዋታዎችን ከመዝናኛ እና ከዕረፍት ሰዓት ጋር ሊያያይዙ ስለሚችሉ በክፍል ውስጥ ጨዋታዎችን እንዳይጠቀሙ ይጠነቀቁ ይሆናል። ይሁን እንጂ ጨዋታዎች ለማስተማር እጅግ በጣም ውጤታማ መሣሪያ ሊሆኑ ይችላሉ። በጨዋታ ላይ የተመሠረተ ትምህርት መማር ይበልጥ አስደሳች፣ አሳታፊ እና የማይረሳ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል። ከጨዋታዎች መማር ከአንድ አካል (ከመምህሩ) ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ተጨዋቾች እንዲሁም ግለሰቦቹ በጨዋታ ወቅት በራሳቸው በመሞከር ይማራሉ። ጨዋታዎች ማህበራዊ እድገትን እና በራስ የመማር ክህሎትን በመደገፍ ከመረጃ በላይ መልዕክት ለማስተላለፍ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። በተጨማሪም ለትናንሽ ልጆች የአቻ ለአቻ አስተያየት በመስጣጣት እና ቁልፍ መልእክቶችን በማጠናከር ለትንንሽ ልጆች ባህሪያትን ለማስተማር ምቹ መሳሪያ ናቸው።

*መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል:* በእናንተ ማህበረሰብ ውስጥ ልጆች ምን አይነት ጨዋታዎችን ይጫወታሉ? ከእነዚህ ጨዋታዎች ምን ምን ክህሎቶችን ይማራሉ?

**ጥቅሞች:** ጥናቶች እንደሚያሳዩት ጨዋታዎች ተማሪዎችን የሚያሳትፉ እና የሚያነሳሱ ውጤታማ የመማሪያ መሣሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ከትምህርታዊ ገለፃዎች ጋር ሲነፃፀሩ ጨዋታዎች የረጅም ጊዜ ዕውቀት ማቆየትን በእጅጉ ሊያሻሽሉ ይችላሉ። በተጨማሪም አሳታፊ ካልሆነ የመማር ስልት ይልቅ ጤናማ ልማዶችን በማስፋፋት ረገድ ይበልጥ ውጤታማ ናቸው፤ በመሆኑም የባሕሪ ለውጥን ማበረታታቱ ጠቃሚ መሣሪያዎች ናቸው። በተጨማሪም ጨዋታዎች በክፍል ውስጥ ሌሎችንም ጥቅሞች ሊያስገኙ ይችላሉ፤ ለምሳሌ በፅሞና የመከታተል ደረጃን መጨመርና ልጆች ደንቦችን የማክበር ችሎታቸውን ማሻሻል ይችላሉ። ለተማሪዎች ከሚያስገኛቸው ሌሎች ጥቅሞች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል:

- ✓ **ግብ የማስቀመጥ ክህሎት:** አንድ ጨዋታ ተማሪዎቹ የግለሰብ ወይም የቡድን ግቦችን ለማስቀመጥ እና ግቦችን ለማሳካት የማቀድ እድል ይሰጣቸዋል። ግብ ማውጣት የይዘቱን ባለቤትነት እና ኢጥገኛነት (ንራስን ችሎ መስራትን) ያበረታታል ።
- ✓ **እርስ በርስ የመግባባት ክህሎት:** ተማሪዎች በቡድን ስራ እና በውድድር በተለየ መንገድ አቻ ለአቻ በመስራት ጠቃሚ ልምዶች ያገኛሉ። የአቻ ለአቻ ግብረ-መልሶች ድርጊቶቻቸውን፣ ማኅበራዊ እድገታቸውንና ባህሪያቸውን ያሳያል/ይናገራል፡፡
- ✓ **በራስ የመማር ክሎታ:** ተማሪዎች ጨዋታ በመጫወት ሂደት ላይ አዳዲስ እውቀት እና ክህሎትን ሙከራ በማድረግ የበለጠ በራስ መተማመን ስሜት ማግኘት ይችላሉ ።

- ✓ **የመሪነት ክህሎት:** በጨዋታ ውስጥ ተማሪዎች በተለያዩ ጉዳቾች ላይ የመምራት እና ጨዋታን በራሳቸው እና በለሌሎች ተፅዕኖ ለማሳደር እድል ይኖራቸዋል።

*__መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል:__* በጨዋታ ላይ የተመሠረተ የመማር ሂደት ለተማሪዎች ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሌሎች ጥቅሞች ማሰብ ይችላሉ? ለአስተማሪዎችስ የሚኖረው ጥቅም አለ?

**ውጤታማ አጠቃቀም:** ጨዋታዎች በክፍል ውስጥ ዋጋ እንዲኖራቸው አስተማሪው አሳታፊ እና ጠቃሚ የሆኑ ጨዋታዎችን ማዘጋጀት እና መጠቀም አለበት፤ በተጨማሪም ተማሪዎቹ በሚማሩት ነገር ላይ የበለጠ የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማቸው ለማድረግ ጨዋታዎቹ በራስ የመተማመን ስሜትና እርካታ እንዲኖራቸው ማድረግ ይኖርባቸዋል። አስተማሪው ጨዋታ ከመጠቀሙ በፊት ሊጠይቃቸው የሚገቡ አራት ቁልፍ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው:-

- ✓ **ትኩረት:** ይህ ጨዋታ ተማሪዎቹ ጨዋታው እስኪያበቃ ድረስ እንዲመሰጡ እና አስከመጨረሻው ፍላጎት እንዲያሳዩ ያደርጋል? በዚህም ምክንያት ጨዋታዎች ዕድሜን ያገናዘቡ መሆን አለባቸው። ጨዋታው ቀላል ከሆነ ተማሪዎቹ ሊሰለቹ ይችላሉ። ጨዋታው በጣም ከባድ ከሆነ ተማሪዎቹ ከአቅማቸው በላይ ሊሆኑና እንደጠፋባቸው ይቀርና ምንም ዓይነት ስሜት ላይኖራቸው ይችላል። በተጨማሪም በእኩዮች መካከል ያለውን ፉክክር ወይም ትብብር መጠቀም ተማሪዎች የበለጠ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ሊያበረታታ ይችላል ።
- ✓ **ጠቃሚነት፥** ይህ ጨዋታ በዚህ ክፍለ-ጊዜ ከሚሰጠው መማሪያ ይዘት እና ግቦች ጋር ይጣጣማል? ጨዋታው ተማሪዎቹ በአሁኑ ወቅት በትምህርት ቤት ከሚማሩት ጋር የሚስማማ እና ይዘቱን ትርጉም ባለው መንገድ እንዲለማመዱ እድል ይሰጣቸዋል ፡፡
- ✓ **በራስ መተማመን:** ተማሪዎቹ በጨዋታ ወቅት አዲሱን መረጃ እና ክህሎት ለመለማመድ ይችሉ ይሆን? በጨዋታ አማካኝነት ተማሪዎች በእኩዮች አስተያየት ትክክለኛውን መንገድ በሚያጠናክር መንገድ አዲሱን መረጃ እና ባህሪ ሙከራ ማድረግ ይችላሉ። በዚህ ሙከራ አማካኝነት፣ ተማሪዎች ቁልፍ መልዕክቶችን በማካፈል እና የታለሙ ባህሪያትን በማከናወን የበለጠ መተማመን ማግኘት ይችላሉ።
- ✓ **እርካታ:** ተማሪዎቹ ጨዋታ በሚጫወቱበት ጊዜና ከተጫወቱ በኋላ እርካታ ይሰማቸዋልን? ተማሪዎች መመሪያውን በግልጽ ከተረዱና ጨዋታው ፍትሐዊ እንደሆነ ከተሰማቸው በአንድ ጨዋታ ይበልጥ ይረካሉ። ጨዋታው እንደ ሥራ ወይም እንደ ሸክም ሆኖ ሊሰማቸው አይገባም ። ከዚህ ይልቅ አስደሳች እና አዝናኝ ሊሆን ይገባል ።

በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የተካተቱት ሁለቱ ጨዋታዎች የተዘጋጁት ቀደም ሲል በአዕምሯችን ይዘናቸው በነበሩት ጉዳዮች ነው። ይሁን እንጂ አስተማሪዎች የራሳቸውን ተማሪዎች በደንብ የሚያውቁ ከመሆኑም በላይ ይበልጥ ጠቃሚና አስደሳች እንዲሆኑ ለማድረግ በጥሩ ሁኔታ ለተማሪዎቻቸው አስማምተው/አሻሽለው እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ።

## 4.3 ንፁህ የካፒቴን ስሌዳ ጨዋታ

*40 ደቂቃዎች*

*ተሳታፊዎቹን በቡድን መከፈል እና በመመሪያው መሰረት ጨዋታውን እንዲጫወቱ ማድረግ ፡፡.*

ጨዋታዎችን በክፍል ውስጥ ከመጠቀም በፊት አስተማሪዎች ጨዋታዎችን እንዴት እንደሚጫወቱ ማወቁ አስፈላጊ ነው ፡፡ አሁን በቡድን ተከፋፍለን ከተማሪዎች ጋር የምንጠቀምበትን የሰሌዳ ጨዋታ እንጫወታለን፡፡

*የሰሌዳ ጨዋታ መመሪያዎች*

1. ተሳታፊዎችን ከ4-6 ሰዎች በመሆን በአንድ ቡድን ውስጥ እንዲገቡ መንገር ፡፡
2. እያንዳንዱ ቡድን **ንፁህ ካፒቴን የሰሌዳ መጫወቻ** እና የጨዋታ ካርዶቹ እንዳላቸው ያረጋግጡ፡፡
3. ለተሳታፊዎች ማንኛውም ጥያቄ ካለ ወይም ማንኛውም አይነት ግልጽ ያልሆነ ነገር ካለ ለማየት **በአስተማሪው መጽሐፍ** (ክፍል 4) ውስጥ ከ2-5 ኛ ክፍል ያለውን የትምህርት እቅድ እንዲያነቡ መንገር፡፡
4. የትምህርት እቅዱን ካነበቡ በኋላ ጨዋታውን ይጫወታሉ! ከጨዋታ ሰሌዳው ጋር የተያያዙትን መመሪያዎች መከተል አለባቸው፡፡
   - ጨዋታውን ከ2-6 ሰዎች ጋር በመሆን መጫወት ይቻላል፡፡ ማንበብ ለሚቸገሩ ተማሪዎች፣ በእያንዳንዱ የጨዋታ ቡድን ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ማንበብ የሚችል እና ሌሎች ተጫዋቾችን ማገዝ የሚችል ቢያንስ 1 ተጫዋች እንዲኖር ይመከራል፡፡
   - ሁሉም ተጫዋቾች ምልክቶቻቸውን “መጀመሪያ” ላይ አድርገው ይጀምራሉ፡፡ ሁሉም ካርዶች ከቦርዱ በጎን በኩል ካለው በየቀለማቸው መቀመጥ አለባቸው ፡፡
   - እያንዳንዱ ተጫዋች በመጀመሪያ ወይነጠጅ/ሐምራዊ ካርድን ይመርጣል። ከፍተኛ ቁጥር ያገኘ ተማሪ መጀመሪያ በመሄድ በወይነጠጅ/ሐምራዊ ካርዱ ላይ የተፃፉትን የቦታዎች ብዛት ያንቀሳቅሳል። ሌሎች ተጫዋቾች ከጀማሪው ወደ ቀኝ አቅጣጫ አንድ በአንድ በመቀጠል በወይነጠጅ/ሐምራዊ ካርዳቸው ላይ የቦታዎችን ብዛት ያንቀሳቅሳሉ፡፡ በወይነጠጅ/ሐምራዊ ካርዱን ከተጠቀሙ በኋላ እንደገና ከተከማቸበት ስር  መልሰው ያስቀምጣሉ፡፡
   - ምልክታቸው በሰማያዊ ቦታው  ላይ ካረፈ ሰማያዊ “ንፁህ”ካርድ ይመርጡና ከካረዱ ጀረባ የተፃፉ መመሪያዎቹን ይከተላሉ። ሁሉም ሰማያዊ ካርዶች ተጫዋቹን ወደ ፊት ያራምዳሉ ወይም ሌላ ሰማያዊ ካርድ ለመሳብ ተጨማሪ ተራ ይሰጣሉ፡፡
   - ምልክታቸው ቡናማ ቦታ ላይ ካረፈ  ቡናማ “ቆሻሻ”ካርድ ይመርጡና  ከካረዱ ጀረባ የተፃፉ መመሪያዎቹን ይከተላሉ፡፡ ሁሉም ቡናማ ካርዶች ተጫዋቹን ወደ ኋላ ይመልሳሉ ወይም ቀጣዩን ተራ ያሳጣሉ። ወይም ደግሞ በቀጣዩ ተራ ሌላ ቡናማ  ካርድ በሳብ ያስፈልጋቸዋል፡፡
   - ምልክታቸው በአረንጓዴ ቦታ ላይ ካረፈ  አረንጓዴ “የጥያቄ” ካርድ ይመርጡና  ከካረዱ ጀርባ የተፃፈውን ጥያቄ ይመልሳሉ ። ሁሉም አረንጓዴ ካርዶች  ጥያቄ እንዲመልሱ ያዛሉ። ሌሎቹ ተጫዋቾች መልሱ ትክክል መሆን/አለመሆኑን ይፈርዳሉ፡፡ መልሱ ትክክል ከሆነ ወደፊት ይራመዳሉ ወይም ሌላ አረንጓዴ ካርድ ለመሳብ ተጨማሪ ተራ ያገኛሉ። መልሱ ትክክል ካልሆነ በዚህ ተራ ወደፊት ወይም ወደኋላ አይንቀሳቀሱም። እንዲሁም በሚቀጥለው ተራ ጥያቄውን እንደገና ይሞክራሉ፡፡
   - በእያንዳንዱ ዙር ተጫዋቾቹ አንድ ካርድ ብቻ ይወስዳሉ፡፡ ሆኖም፣ አንዳንድ ካርዶች ተጨማሪ ተራ ይሰጣሉ፣ ይህም ማለት  አንድ ተመሳሳይ ቀለም  ያልው አዲስ ካርድ ይመርጡና እንደገና ይንቀሳቀሳሉ ፡፡  ተራ ካጡ፣ ተመሳሳይ ቀለም ያለው ሌላ ካርድ ለመምረጥ ቀጣዩ ተራ እስኪደርስ ይጠብቃሉ ፡፡
   - ካርዶችን ከተጠቀሙ በኋላ ካርዶቹ ከተከማቸበት ስር መልሰው ያስቀምጣሉ ፡፡
   - “መጨረሻ” ላይ የደረሰ የመጀመሪያው ተጫዋች ጨዋታውን ያሸንፋል!
5. ተማሪዎቹ በጨዋታው ላይ መሻሻል ማሳየታቸውን ለማረጋገጥ እና ማንኛውም ጥያቄ ለመመልስ ጨዋታውን ሲጫወቱ በቡድኖች መካከል መንቀሳቀስ፡፡
6. *መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል*

- በዚህ ጨዋታ የትኞቹን ችሎታዎች/ብቃቶች ተጠቅሟል?
- ይህ ጨዋታ በ**4.2** ከተጠቀሰው ውስጥ ያሉተን አራት ጥያቄዎች ትኩረት ፣ ጠቀሜታ/አስፈላጊነት ፣ በራስ መተማመን እና እርካታ ላይ መልስ ይሰጣል ብላችሁ ታስባላችሁ?
- ይህንን ጨዋታ እንዴት መለወጥ ወይም ማሻሻል ይቻላል?

## 4.4 የሥነ-ንጽህና ጀግኖች ፈታኝ ጨዋታ *30 ደቂቃዎች*

*መረጃውን ከተሳታፊዎች ጋር መግምገም ፡፡ ይህንን ክፍል በትምህርታዊ ገለፃ ወይም በውይይት መደገፍ ይቻላል፡፡*

የሰሌዳ ጨዋታ በአንድ ክፍል የመማሪያ ክፍለ ጊዜ ውስጥ በቀላሉ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሲሆን ተማሪዎች ከአንድ ጊዜ በላይ ሊጫወቱት ይችላሉ፡፡ ለጤና እና የዋሽ ክበባት ጨዋታቸው ሰፋ ያለ እና ከ 10 ቀናት በላይ በሚፈጅ ጊዜ ይካሄዳል፡፡ **የሥነ-ንፅህና ጀግኖች ፈታኝ ጨዋታ** ውድድርን እና የቡድን ስራዎችን በመጠቀም የክበቡን አባላት ለማነሳሳት ይጠቅማል ፡፡ ይህን ጨዋታ ለማጠናቀቅ በርካታ ቀናት ሊወስድ ስለሚችል እኛ ሙሉ በሙሉ አንጫወትም ፡፡

*የፈተኝ ጨዋታ መመሪያዎች*

1. ተሳታፊዎችን ከ4-8 ሰዎች በመሆን በአንድ ቡድን ውስጥ እንዲገቡ መንገር ፡፡
2. እያንዳንዱ ቡድን **ለሥነ-ንፅህና ጀግኖች ፈታኝ ጨዋታ** ሰንደቅ Poster እንዳለው ማረጋገጥ ፡፡
3. ተሳታፊዎች ማንኛውም አይነት ጥያቄ ካላቸው ወይም ግልጽ ያልሆነ ነገር እንዳለ ለመመልከት የክበብ አባላትን እቅድ **በአስተማሪው መጽሐፍ** (ክፍል 5) ውስጥ እንዲያነቡ መንገር ፡፡
4. አንድ ተሳታፊ "የክበብ አስተባባሪ" ሚና የሚጫወት ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ "ተማሪዎች" ይሆናሉ፡፡ ከሌሎች ጋር ጨዋታውን እንዴት እንደሚጫወቱ የክለቡ አስተባባሪ ይገመግማል ፡፡
    - የተማሪዎችን ስም በዝርዝሩ በሰንደቁ (The poster) ላይ መጻፍ፡፡ ሰንደቁ (The poster) ለእያንዳንዱ ተማሪ ከፈታኝ ጥያቄዎች ነጥቦችን ለመመዝገብ ይጠቅማል፡፡
    - ለፈታኝ ጨዋታው አስተባባሪ መምረጥ፡፡ ይህ ሰው የክለቡ አስተባባሪ ወይም ፈተናው ውስጥ የማይሳተፍ ተማሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ አስተባባሪ ፈተናዎችን፣ የፍርድ ሂደት ማጠናቀቂያ እና የሽልማት ነጥቦችን ያስታውቃል፡፡
    - ተማሪዎች በእያዳንዱ ቀን ለማጠናቀቅ የተለየ ፈተና ይኖራቸዋል፡፡ አንዳንድ ፈተናዎች በግል የሚሰሩ ናቸው፣ አንዳዶቹ ደግሞ በቡድን ሊጠናቀቁ ይችላሉ፡፡ ፈተናውን በቡድን ካጠናቀቁ ሁሉም የቡድን አባላት ተመሳሳይ ነጥቦችን ያገኛሉ።
    - ፈተናውን በወቅቱ ካላጠናቀቁ 0 ነጥብ ያገኛሉ፡፡
    - ፈተናውን በግማሽ ካጠናቀቁ 5 ነጥቦችን ያገኛሉ፡፡
    - ሙሉ ፈተናውን በወቅቱ ካጠናቀቁ 10 ነጥቦችን ይቀበላሉ፡፡ በአንድ ጨዋታ ከፍተኛው የነጥብ ብዛት 100 ነው (ለእያንዳንዱ10 ነጥብ 10 ፈተናዎች አሉት)፡፡
    - ፈተናውን ከት/ቤት ውጭ ካጠናቀቁ (እንደ ተፈና 6) ፣ ነጥቦቹን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚቻል መወሰን። ለምሳሌ ፣ ሌላ ሰው ሊያረጋግጥላቸው ይችላል፣ ወይም አጠናቀዋል የሚል የተፈረመ ወረቀት ይዘው መምጣት ይችላሉ፡፡

- ከ10 ፈተናዎች በኋላ ነጥቦቹ ይሰበሰባሉ ፡፡ ከፍተኛ ውጤት ያላቸው ሁለቱ ተማሪዎች የሥነ-ንፅህና ጀግኖች ናቸው፡- በትምህርት ቤት ዙሪያ የሚለብሱ ሜዳሊያ ያገኛሉ ፡፡ ከ 2 በላይ አሸናፊዎች ካሉ ሜዳሊያውን እየተቀያየሩ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ እንደ አማራጭ፣ ተጨማሪ የማበላለጫ ነጥቦችን በመጠቀም አሸናፊውን መለየት ፈተናዎችን ማቅረብ ፡፡

5. ልምምድ ለማድረግ “የክለብ አስተባባሪው” ለ “ተማሪዎች” እንደምሳሌ ከ1-2 ፈተናዎችን በመምረጥ ያጠናቅቃል ፡፡ ተሳታፊዎች ሌሎች ሁሉንም ፈተናዎች በጋራ ያነባሉ ፡፡
6. ቡድኖቹ ጨዋታውን ሲገመግሙ ፣ መሻሻል መኖሩን ለማውቅ በክፍሉ ውስጥ መንቀሳቀስ እና ጥያቄዎች ካሉ መልስ መስጠት ፡፡
7. *መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል:*

- ይህ ጨዋታ የትኞቹን ችሎታዎች/ብቃቶች ተጠቅሟል?
- ይህ ጨዋታ **ከ4.2** ውስጥ ያሉተን አራት ጥያቄዎች ትኩረት ፣ አስፈላጊነት ፣ በራስ መተማመን እና እርካታ ላይ መልስ ይሰጣል ብላችሁ ታስባላችሁ?
- ይህንን ጨዋታ እንዴት መለወጥ ወይም ማሻሻል ይቻላል?

አሁን ለእነዚህ ፕሮግራሞች ሦስቱን ተግባራት ማለትም ትግበራ መጽሐፍን ፣ የንጹህ ካፕቴን የሰሌዳው ጨዋታን እና ፈታኝ ጨዋታን ገምግመናል ፡፡ በመጨረሻው የሥልጠና ክፍለ ጊዜ የተማርነውን እንገመግማለን ፣ እንዴት ወደ ትምህርት ቤቶቹ እንደሚወርድ እቅድ እና ማንኛውንም አይነት ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ሐሳብን እናንጽባርቃለን፡፡

# ክፍል 5፡ እቅድ ማዘጋጀት

## 5.1 በጥልቀት ማሰብ እና አስተያየት መስጠት የሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች

*15 ደቂቃዎች*

*በጥንድ በጥንደ እየሆኑ በጥያቄዎቻቸው ላይ በጋራ እንዲወያዩ 5 ደቂቃ መስጠት። ከቆይታ በኋላ ሁሉንም ሰዎች ወደ አንድ በመመለስ ሁሉንም የቡድን ጥያቄዎች መጠየቅ። መልሶቹን በትልቁ ወረቀት (flip chart) ላይ መፃፍ ወይም ተሳታፊዎች እርስ በእርስ ምላሽ እንዲሰጡ መጠየቅ ፡፡*

- ለጥንዶች፡ ከጨዋታዎች ውስጥ የትኛው ጨዋታ (የትግበራ መጽሐፍ ፣ የቦርድ ጨዋታ ፣ ፈታኝ ጨዋታ) በእናንተ ማህበረሰብ ውስጥ በተሻለ ሁኔታ ይሠራል ብላችሁ ታስበባላችህ? ይህንን ስልጠና በትምህርት ቤት ደረጃ ለማድረስ ምቾት ይሰማችኋል?
- ለሁሉም ቡድን፡ በአሰልጣኞች ስልጠና (ToT) ወቅት ምን አዳዲስ ክህሎቶችን ወይም መረጃዎችን ተምራችኋል? ምን መሻሻል አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ?

## 5.2 ለጨዋታዎች የድርጊት መረሐ-ግብር ማዘጋጀት

*30 ደቂቃዎች*

*መረጃውን ከተሳታፊዎች ጋር መገምገም ፡፡ ይህንን ክፍል ትምህርታዊ ገለፃ ወይም በውይይት መደገፍ ይቻላል ፡፡*

ዛሬ ይህን የአሰልጣኞች ስልጠና ከጨረሱ በኋላ፤ ተሳታፊዎቹ ስልጠናውን ወደ ሚቀጥለው ደረጃ ያወረዳሉ/ያስኬዳሉ ተብሎ ይጠበቃል ፡፡ መረጃው አሁንም በአእምሯቸው ውስጥ ሳይወጣ/ሳይረሳ በወር ጊዜ ውስጥ ሥልጠናውን ወደታች ለማውረድ ዓላማ ማድረግ አለባቸው።. ስልጠናውን በሁሉም ደረጃዎች ወደታች የማውረድ/ማስኬድ ስራ ከ1-3 ወራት ውስጥ መጠናቀቅ አለባቸው ፡፡ ስልጠናውን ለመስጠት የሚከተሉትን መመሪያዎች መጠቀም ይቻላል፡

| አሰልጣኝ | ተሳታፊዎች | የጊዜ ገደብ | ይዘት |
|---|---|---|---|
| የናላ ፋውንዴሽን የፕሮገራም ሰራተኞች | የወረዳ ተወካዮች | - | ከስልጠና መመሪያው ውስጥ ከክፍለ 1-5 |
| የወረዳ ተወካዮች | የትምህርት ቤት ተወካዮች | ከናላ የአሰልጣኞች ስልጠና  በኋላ ከ7-30 ቀናት ውስጥ | ከስልጠና መመሪያው ውስጥ ከክፍለ 1-5 |
| የትምህርት ቤት ተወካዮች | መምህራን | ከወረዳ አሰልጣኞች ስልጠና  በኋላ ከ7-30 ቀናት ውስጥ | ከስልጠና መመሪያው ውስጥ ከክፍለ 1-4 |
| መምህራን | ተማሪዎች | ከትምህርት ቤት ስልጠና  በኋላ ከ7-30 ቀናት ውስጥ | በአስተማሪው  መጽሐፍ ውስጥ የትምህርት መረሐ-ግብር |

ተሳታፊዎች ወደ ታች ለማውረድ የሚያዘጋጅቱን የትምህርት ቤቱን የድርጊት መረሐ-ግብር ለማገዝ በየወረዳ ወይም በየት/ቤት ቡድን በመስራት የድርጊት መርሃ ግብር እንዲያዘጋጁ የተወሰነ ጊዜ መስጠት ፡፡

*የድርጊት መርሃ ግብር መመሪያዎች*

1. ተሳታፊዎች በየወረዳቸው ወይም በየትምህርት ቤታቸው ወደ ቡድን ውስጥ እንዲገቡ መንገር ፡፡
2. በወረዳ ደረጃ፣ **በአባሪ-3** ላይ ያለውን የድርጊት መርሃ ግብር እንዲሞሉ ማድረግ ፡፡
3. በትምህርት ቤት ደረጃ፣ **በአባሪ-4** ላይ ያለውን የድርጊት መርሃ ግብር እንዲሞሉ ማድረግ ፡፡
4. ቡድኖቹ እቅዳቸው በሚያያዘጋጁበት ወቅት ስራቸውን ለመከታተል በክፍል ውስጥ መንቀሳቀስ እና ጥያቄዎች ካሉ መልስ መስጠት ፡፡
5. *መጠየቅ እና መልሶችን መቀበል*
   - በሚቀጥለው ወር ጊዜ ውስጥ ሥልጠናውን ወደታች ማውረድ ትችላላችሁ?
   - ስልጠናውን ወደታች ለማውረድ ምን ዓይነት ዝግጅቶችን ማድረግ ያስፈልጋችኋል?
   - በአባሪ 5-6 ውስጥ ያሉተን የክትትል ቅጾችን መመልከት ፡፡ ለውጡን ለመከታተል እነዚህን ቅጾች እንዴት መጠቀም ትችላላችሁ? በተለየ መንገድ መከታተል ትመርጣላችሁ?

***ማስታወሻ**: ፕሮግራሙ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ሲጀመር፣ ከ3-5ኛ ክፍል ያሉ መምህራን ለተማሪዎቻቸው በቂ የሰሌዳ መጫወቻ እንዲኖር እንዲሁም ሲያስተምሩ በክፍሉ ውስጥ በተማሪዎቹ መካከል መዘዋወር አለባቸው፡፡*

## 5.3 አዕምሮን የሚያነቃቁ ሐሳብ (Brainstorming ) *40 minutes*

*መረጃውን ከተሳታፊዎች ጋር መገምገም ፡፡ ይህንን ክፍል በትምህርታዊ ገለፃ ወይም በውይይት መደገፍ ይችላሉ ፡፡*

የአሰልጣኞች ስልጠናውን ከማጠናቀቃችን በፊት በተወሰኑ የመጨረሻ ጉዳዮች ላይ አዕምሮን የሚያነቃቁ ሐሳቦችን እናነሳለን ከዚይ በኋላ በቡድን ሁነን እንወያይባቸዋለን ፡፡

*የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይቶች መመሪያዎች*

1. ተሳታፊዎችን ከ10-15 ሰዎችን በቡድን መከፈል ፡፡
2. ለቡድኖች የመወያያ ርዕስ መስጠት ፡፡ ከእነዚህ ርዕሰ-ጉዳዮች ወስጥ የተውሰኑት ከድርጊት መረሐ ግብራቸው ጋር የተያያዙ መሆን አለባቸው ፡፡ ርዕሶችን በየ 3-5 ደቂቃዎች መቀያየር ፡፡
   - በስልጠናችሁ ላይ እንዲገኙ እንዴት ታበረታታላችሁ?
   - በት/ቤቶች ውስጥ የፕሮግራሙን መሻሻል ወይም ለውጥ እንዴት ትከታተላላችሁ?

- አንድ ትምህርት ቤት (ወይም በትምህርት ቤቱ ውስጥ ያሉ መምህራን) ጨዋታዎቹን የማይጠቀሙበት ከሆነ ምን ታደርጋላችሁ?
- በትምህርት ቤት ውስጥ ለእጅ መታጠቢያ የሚሆን ውሃ እና ሳሙና መኖሩን እንዴት ማረጋገጥ እንችላለን?
- በፕሮግራሙ ውስጥ ወላጆችን ለማሳተፍ ሀሳቡ አላችሁ?
- ፕሮግራሙን ከመተግበር ጋር በተያያዘ ያስተዋላችኋቸው ተግዳሮቶች ወይም ችግሮች ምንድናቸው?

3. ውይይቶችን ለመመልከት እና ለማበረታታት በክፍሉ ውሰጥ መንቀሳቀስ ፡፡
4. ከእያንዳንዱ ጥያቄ በኋላ ጥቂት ሰዎች ምላሻቸውን ለሁሉም እንዲያቀርቡ መጠየቅ፡፡

## 5.4 መዝጊያ

*15 ደቂቃዎች*

*አመቻች አምስቱን ቁልፍ መልዕክቶች እንዲዘረዝሩ በማድረግ እና በየመሐሉ በማስጨብጨብ መልመጃ በማሰራት ይመራቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመዝጊያ ክፍለ-ጊዜ አጭር አስተያየት ወይም ግብረ-መልስ ለመቀበል ሊያገለግል ይችላል ፡፡*

ተሳታፊዎች በአሰልጣኞች ስልጠና ላይ በመሳተፋቸው እና ማህበረሰባቸው ጤናማ እንዲሆን ለማድረግ በመነሳሳታቸው ምስጋና ማቅረብ ፡፡

*ለቀልዶች የሚሆኑ መመሪያዎች*

1. አመቻቹ "አሁን የአሰልጣኞች ስልጠናውን በ5ቱ ቁልፍ መልዕክቶች እና በጭብጨባ እንዘጋዋለን" ይላል ፡፡
2. አሰልጥኙ ከቁልፍ መልዕክቶች ወስጥ አንዱን (ንፁህ እጆች) ይላል ከዚያ ሁሉም ሰው አንድ ጊዜ ያጨበጭባል ፡፡
3. ሌላ ቁልፍ መልእክት እንዲናገር ከተሳታፊ ይጠቁምና ሁሉም ሰው እንደገና ያጨበጭባል ፡፡
4. ያሰው ሌላ ቁልፍ መልእክት እንዲናገር ሌላ ተሳታፊ ይጠቁማል ወዘተ ፡፡
5. እንደገና መደጋጋም ነገር ግን በፍጥነት።

***መጠየቅ***

- በአሰልጣኞች ስልጠና ላይ በተጠቅምናቸው መመሪያዎች ላይ ማንኛውም አይነት ጥያቄ ካለ? የመጨረሻ ሀሳቦች ወይም አስተያየቶች?

# አባሪ 1፡ የእጅ አስተጣጠብ ሂደቶች

**ጠቀሜታ፥** የእጅ አስተጣጠብ ሂደቶችን ለተማሪዎች ለማሳየት እና ሞዴል ለማድረግ ይህንን ገጽ እንደ መመሪያ መጠቀም ይቻላል።


እጅን ለ 20 ሰከንድ በውሃ እና በሳሙና መታጠብ እና ሁሉንም የእጆቹን ክፍሎች ማዳረስ ይመከራል ፡፡



1. እጆቻችሁን በውሃ ማርጠብ።



2. አረፋው እስኪወጣ ድረስ እጅን በሳሙና ማሸት።




3. የአንደኛውን እጅ መዳፍ ከሌላኛው እጅ መዳፍ ጋር ማሸት።



4. እጅን እያቀያየሩ የመዳፍን ጀርባ ማሸት፡፡




5. የአንደኛውን እጅ ጣቶች በሌላኛው እጅ ጣቶች በማጠላለፍ ማሸት።



6. የሁለት እጆችን ጣቶች ጫፍ ፊት ለፊት በማቆላለፍ ማሸት፡፡



7. አወራ ጣትን በእጅ መዳፍ ጨበጦ በማሽከርከር ማሸት



8. በእጅ ጣቶች ጫፍ መዳፉን ማሸት፡፡




9. እያንዳንዱን የእጅ አንጓ በተቃራኒ እጅ መሸት ፡፡



10. ሳሙናው እስኪለቀው ድርስ እጆችን በውሃ ማለቅለቅ።



11. እጆችን አየር ላይ በማወዛወዝ ወይም ንጹህ ፎጣ በመጠቀም ማዳረቅ።



12. እጆቻችሁ አሁን ንፁህ ናቸው!

# አባሪ 2፡ እጅን መታጠብ + ፊትን መታጠብ


**ጠቀሜታ:** ለትንንሽ ልጆች ሂደቶችን ለመቅረፅ ይህንን ገጽ እንደ መመሪያ መጠቀም ይቻላል፡፡ ሂደቶቹ ቀለል ያሉ እና የፊት መታጠብንም አካተዋል። ዓላማው ልጆች ፊትን መታጠብ የዕለት ተዕለት ልማዳቸው እና የጠዋትና ማታ የተግባራቸው አካል ማድረግ ነው ፡፡



1. እጆቻችሁን በውሃ ማርጠብ።



2. አረፋው እስኪወጣ ድረስ እጅን በሳሙና ማሸት።



3. የአንደኛውን እጅ መዳፍ ከሌላኛው እጅ መዳፍ ጋር ማሸት።



4. የአንደኛውን እጅ አጣቶች በሌላኛው እጅ ጣቶች በማጠላለፍ ማሸት።



5. ፊትን ለማጠብ በሳሙና የታጠቡ እጆችን መጠቀም፡፡ ፊትን በምትታጠቡበት ጊዜ ሁሉ ዓይናችሁን  መጨፈን ይኖርበችኋል፡፡




6. እጆችን በውሃ ማለቅለቅ።



7. ፊትን በዉሃ በማለቅለቅ ሳሙናው ሙሉ በሙሉ መልቀቁን ማረጋገጥ።



8. እጆችን አየር ላይ በማወዛወዝ ወይም ንጹህ ፎጣ በመጠቀም ማዳረቅ።



9. እጆቻችሁ እና ፊታችሁ አሁን ንፁህ ናቸው!

# አባሪ 3፡ በወረዳ ደረጃ የድርጊት መርሃ-ግብር

**ጠቀሜታ:** የወረዳው ተወካዮች ፕሮግራሙን በወረዳቸው ውስጥ እንዴት እንደሚጀመር ዕቅድ ለማዘጋጀት ይህንን ቅጽ ይጠቀማሉ ፡፡

| ለጨዋታዎች የድርጊት መርሃ-ግብር (ወረዳ) | |
|---|---|
| የወረዳው ስም: | |
| የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት: | |
| ለት/ቤት ተወካዮች ስልጠና ለመስጠት የታሰበበት ቀን: | |
| በትምህርት ቤቶች ፕሮግራሙን ለመጀመር የታሰበበት ቀን: | |
| የት/ቤቱ ተወካዮች ሥልጠናው ላይ እንዲገኙ ለማበረታታት ምን ማድረግ ይጠበቅባችኋል? | |
| *1.*<br>*2.*<br>*3.* | |
| የፕሮግራሙን ሂደት ለመከታተል ምን አይነት እርምጃዎችን ትወስዳላችሁ? | |
| *1.*<br>*2.*<br>*3.* | |
| ፕሮግራሙን የማይጠቀሙ ትምህርት ቤቶች ካሉ ምን አይነት እርምጃዎችን ትወስዳላችሁ? | |
| *1.*<br>*2.*<br>*3.* | |

# አባሪ 4፡ በትምህርት ቤት ደረጃ የድርጊት መርሃ-ግብር

**ጠቀሜታ፡** የትምህርት ቤት ተወካዮች ፕሮግራሙን በትምህርት ቤታቸው ውስጥ እንዴት እንደሚጀመር ለማቀድ ይህንን ቅጽ ይጠቀማሉ ።

| | ለጨዋታዎች የድርጊት መርሃ-ግብር (ወረዳ) |
|---|---|
| **የትምህርት ቤቱ ስም:** | |
| **የተማሪዎች ቁጥር:** | |
| **ለመምህራን ስልጠና ለመስጠት የታሰበበት ቀን:** | |
| **በትምህርት ቤት ውስጥ ፕሮግራሙን ለመጀመር የታቀደበት ቀን:** | |
| **በመምህራን ስልጠና ላይ ተሳታፊዎች እንዲገኙ ለማበረታታት ምን ማድረግ ይጠበቅባችኋል?** | |
| *1.*<br><br>*2.*<br><br>*3.* | |
| **የፕሮግራሙን ሂደት ለመከታተል ምን አይነት እርምጃዎችን ትወስዳላችሁ?** | |
| *1.*<br><br>*2.*<br><br>*3.* | |
| **ፕሮግራሙን የማይጠቀም መምህር ካለ ምን አይነት እርምጃዎችን ትወስዳላችሁ?** | |
| *1.*<br><br>*2.*<br><br>*3.* | |

# አባሪ 5፡ በወረዳ ደረጃ የክትትል ቅጽ

**ጠቀሜታ :** የወረዳው ተወካይ ይህንን ቅጽ በትምህርቱ ሴሚስተር መጨረሻ ላይ ይጠቀምበታል ፡፡

| **I. ትቀል መረጃ** | |
|---|---|
| **1**. ቀን: | |
| **2**. ስም: | |
| **3**. ስልክ/ኢሜል: | |
| **4**. ወረዳ/ዞን: | |
| **5**. በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ት/ቤቶች ብዘት: | |

| **II. ስልጠና** | |
|---|---|
| **6**. የዞን ስልጠና ቀን: | |
| **7**. በወረዳ ደረጃ ለት/ቤቶች የስልጠና ቀን: | |
| **8**. በወረዳ ስልጠና የተጋበዙ ተሳታፊዎች ብዛት: | |
| **9**. በወረዳ ስልጠና የተገኙ ተሳታፊዎች ብዛት፡ | |

| **III. ትግበራ** | |
|---|---|
| **10**. ሁሉንም (3ቱን) ጨዋታዎች የተገበሩ ት/ቤቶች ብዘት: | |
| **11**. ከ1-2 ጨዋታዎችን የተገበሩ ት/ቤቶች ብዛት: | |
| **12**. ትግበራ ያልጀመሩ ትምህርት ቤቶች በዛት | |
| **13**. ለክትትል የተጎበኙ ት/ቤቶች ብዛት: | |
| **14**. ከፕሮግራሙ መጀመር በኋላ በባህሪ ለውጥ፡ | |

| **IV. አስተያየቶች** |
|---|
| |

**15.** በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች/ችግሮች:

**16:** የት/ቤቱ ተሞክሮዎች (Success story/case study):

# አባሪ 6፡ በትምህርት ቤት ደረጃ የክትትል ቅጽ

**ጠቀሜታ:** የትምህርት ቤቱ ተወካይ ይህንን ቅጽ ለወረዳው ተወካይ ይመልሳል ፡፡

| | |
|---|---|
| **I. ጥቅል መረጃ** | |
| **1**. ቀን: | |
| **2**. ስም: | |
| **3**. ወረዳ: | |
| **4**. የት/ቤቱ ስም: | |
| **5**. በት/ቤቱ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ብዛት: | |
| **II. ስልጠና** | |
| **6**. በወረዳ ለት/ቤት ተወካዮች የስልጠና ቀን: | |
| **7**. በስልጠናው የተሳተፉ የት/ቤት ተወካዮችብዛት: | |
| **8**. የመምህራን ስልጠና ቀን በ/ትቤት: | |
| **9**. በስልጠናው የተገኙ መምህራን ብዛት: | |
| **III. ትግበራ** | |
| **10**. ከ 1-2 ኛ ክፍል  የተማሪዎች ብዛት: | |
| **11**. የትግበራ መጽሐፍን ያጠናቀቁ የተማሪዎች ብዛት:: | |
| **12**. ከ3-5 ኛ ክፍል የተማሪዎች ብዛት: | |
| **13**. የሰሌዳ ጨዋታ የተጫወቱ የተማሪዎች ብዛት: | |
| **14**. በጤና/ዋሽ ክበቦች ውስጥ የተካተቱ የተማሪዎች ብዛት: | |
| **15**. ፈታኝ ጨዋታውን የተጫወቱ የተማሪዎች ብዛት: | |
| **IV. ፕሮግራሙ ከተጀመረ በኋላ ያለው ተጽዕኖ/ለውጥ** | |

| | |
|---|---|
| **16**. ብዙ ተማሪዎች እጃቸውን ሲታጠቡ ታያለህ? | ☐ አዎ, በብዙው ☐ አዎ, በትንሹ<br>☐ የለም ☐ እርግጠኛ አይደለሁም |
| **17**. ንፁህ ፊት ያላቸው ተማሪዎችን ታያለህ? | ☐ አዎ, በብዙው ☐ አዎ, በትንሹ<br>☐ የለም ☐ እርግጠኛ አይደለሁም |
| **18.** በትምህርት ቤቱ ንፅህና ላይ የታየ መሻሻል አለ? | ☐ አዎ, በብዙው ☐ አዎ, በትንሹ<br>☐ የለም ☐ እርግጠኛ አይደለሁም |
| **19.** በትምህርት ቤት ውስጥ የውሃ እና / ወይም የሳሙና አቅርቦት መሻሻል ታይቷል? | ☐ አዎ, ሁለቱም ☐ አዎ, ውሃ<br>☐ አዎ, ሳሙና ☐ የለም<br>☐ እርግጠኛ አይደለሁም |
| **20.** መምህራን ከጤና ጋር የተያያዙ ርዕሰ ጉዳዮችን በሚያስትመሩበት ውቅት የበለጠ በራስ መተማመን ይሰማቸዋል? | ☐ አዎ, በብዙው ☐ አዎ, በትንሹ<br>☐ የለም ☐ እርግጠኛ አይደለሁም |

# መመሪያውን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የዋሉ ማጣቀሻዎች


1. Gardner, H. (1983). Frames of mind: The theory of multiple intelligences. NY: Basics.
2. Gill, Eric (2020). “What is Your Teaching Style? 5 Effective Teaching Methods for your Classroom.” *Resilient Educator*. https://resilienteducator.com/classroom-resources/5-types-of-classroom-teaching-styles/
3. Grasha, A. F. (1994). A matter of style: The teacher as expert, formal authority, personal model, facilitator, and delegator. College teaching, 42(4), 142-149.Heckman, J. J., & Masterov, D. V. (2007). The productivity argument for investing in young children. Applied Economic Perspectives and Policy, 29(3), 446-493.
4. Karbownik, M. S., Wiktorowska-Owczarek, A., Kowalczyk, E., Kwarta, P., Mokros, Ł., & Pietras, T. (2016). Board game versus lecture-based seminar in the teaching of pharmacology of antimicrobial drugs—a randomized controlled trial. FEMS microbiology letters, 363(7).
5. Keller, J. M. (1987). Development and use of the ARCS model of instructional design. Journal of instructional development, 10(3), 2-10.
6. Ogden, S (2013). WASH and the Neglected Tropical Diseases. A Manual for WASH Implementers Ethiopia. Technical Report. WASH NTD. Accessed via http://childrenwithoutworms.org/sites/default/files/ETH%20WASH%20NTD%20Manual.pdf
7. United Nations General Assembly (2015). “Transforming Our World: The 2030 Agenda for Sustainable Development.” Draft resolution referred to the United Nations summit for the adoption of the post-2015 development agenda by the General Assembly at its sixty-ninth session. UN Doc. A/70/L.1 of 18 September 2015.
8. Viggiano, A., Viggiano, E., Di Costanzo, A., et al. (2015). Kaledo, a board game for nutrition education of children and adolescents at school: cluster randomized controlled trial of healthy lifestyle promotion. European journal of pediatrics, 174(2), 217-228.
9. World Health Organization (1998). Resolution 51.11. From 51st World Health Assembly meeting on May 16, 1998.
10. World Health Organization (2015). "Water sanitation & hygiene for accelerating and sustaining progress on neglected tropical diseases: a global strategy 2015-2020."

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር | ናላ ፋውንዴሽን | ሳይት ሴቨር